የመለስ "ትሩፋዎች"

ባለቤት አልባ ከተማ

ኤርምያስ ለገሰ

ከ 50-100

አባል የነበረችው ጣይቱ አሊ (የቀድሞ ትምህረት ሚኒስትር ገነት ዘ ዘመድ) አውጫጭኝ በካድሬዎች የትውስታ ማድማዳ ላይ ተጽፎ ቀር ለተተኪው ካድሬ በቅቅብሎሽ ህግ መሰረት እየተላለፈ አመተ - ተሻግሯል።

የጣይቱን ግምገማ የመሩት ሁለቱ ካህሳዬች ነበሩ።

ቀዩ ካህሳይ፣ "ጣይቱ መጀመራያ የት ትሰሪ ነበር" በማለት ጠየቃት

"ሴቶች ማህበር"

"ከዛ በኋላስ"

"የዞን ስራ አስፈፃሚ"

ጥቁሩ ካህሳይ፣ "ማነው ወደ ዞን ያመጣሽ"

"የዞኑ ፕሮፖጋንዳ ሀላፊ፣ ..."ዴት"... እንደራረግ ነበር "እንደ እያለች መልስ ሰጠች።

"ቀጥሎስ ?"

"የከተማውን ካቢኔ ተቀላቀልኩ። የበኢዴን ስራ አስፈፃሚ ከሆነ የተለየ ግንኙነት ነበረን..." በድጋሚ እፍረቷ መጣ።

ቀዩ ካህሳይ፣ "የእኛ ከሊኢፓትራ! እንኳንም ስሙን አልጠቀሽ።" በእለቱ ተባረረች። ሻንጣዋን ሸከፉ ወደ ቤቷ ሔደች።

ከዛ ቀን ጀምሮ ካድሬው ከጣይቱ ጋር በተናጠል ማውራት ፈራ። አርከበ እቁባይ ወደ መዲናይቱ ተመድበ ሲመጣ መልካም ግንኙነት ፈ ድጋሚ የማህበራት ማደራጃ ቢሮ ሀላፊ አድርጉ ሾማት። ብዙም ሳትቆያ "ተከድኖ ይብሰል" ባለችው ምክንያት አባረራት።

ከሁለት አመታት በኃላ ኢህአዴግ ቢሮ ተመድቤ በምሰራበት አንዲት ጠዋት አለቃዬ ወደ ነበረው ሀላፊ ዮሴፍ ቢሮ ሄድኩኝ። ያለው የቢሮው በር ብርግድ ብሎ ተከፍቷል። ገና ኮቴዬን ሲሰማ ጠርቶ አስቀመ ተግባባን።

ጣይቱ እንግዳ ማረፊያ ሶፉ ላይ ተቀምጣለች። በስጦታ ሰ የተጠቀለለ ነገር እያሳየኝ አሜሪካን ሀገር ለአረፍት ሄዳ መምጣቷን ነ ለጣይቱ አሜሪካን የውሀ መንገድ ነው። አፍታም ሳትቆይ አርከበ ነ እንዴት ደጅ እንዳስጠናትና እንዳንከራተታት በእንባ ታጅባ ዘረገፈ ሀላፊ አፅናናት። ለጓዶች ንገሪያቸው አላት። በመሀል ስልክ መጥቶባት ማ ጀመረ።

እኔና እሷ ተጋጠምን... ፈራኋት...

መጥፎ ስም የማወራው ግራ ሲገባኝ፣ "ትዳር መሰረትሽ ተስማምቶሻል" አልኳት። በአዘነ ስሜት ውስጥ ሆና፣

"ባገባማ ማንም የሚስቱ ጭን መቀት ሲበርድበት አቶኑን ለማስተንፈስ እደክራት-ትኝም" አለች።

"ታዲያ ለምን አታገቢም?"

"እድሜ ለዶንቦስኮ ስሜ ከአዲሳባ እስከ አሜሪካ ጠፉ! የማጠልሸት ዘመቻ ተከፈተብኝ። ስንቱ በእደባባይ የሚሰራው ጉድ እያለ የሰው ይፈተፍታል" አለች።

እውነቷን ነበር።

ከጥቂት ቀን በኋላ በየትኛው መንገድ እንዳለፈች ባላውቅም የአዲሳባ ኢህአዴግ ሴኖች ሊግ የመስራቾች ፕሬዝዳንት ሆና ከእኛ ጋር ተቀላቅላለች፡...

"I am a single lady!" የእሷ ጓደኛና የስራ ባልደረባችን ገጣሚ ፍሬህይወት አያሌው በሳፈችው ግጥም እንደገለፀችው።

***

ይህ ደግሞ በአቶ አሊ አብዶ ካቢኔ ውስጥ የነበረ ካድሬ ግምገማ ነው። ካደሬው ለሌላውም ማስተማሪያ ይሆናል በማለት ባለቤቱን በኤድስ ማጣቱንና አሱም ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖር ሳይደብቅ ይናገራል። ወቅቱ ደግሞ በሻይረስ ያተያዙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ መገለል የሚፈፀምበት ስለነበር የካቢኔ አባሉ ይህን በደፋ በመናገሩ ሁሉም ተገርሚል። ርግጥ ከባለቤቱ መሞትና የሰውየው ቁመና በየቱኑ እየተዳከመ መሄዱን ብዙሀኑ ስለተመለከተ ያልተነገረ ሀሜት ሆኖ ሰንብቷል።

ቀዩ ካህሳይ እንዲህ በማለት ጥርነፋውን ጀመረ፣

"ስማ አስኪ! ስንት ሴቶች በከለሀል? በእንተ ምክንያት የሰንት ሰዎች ቤት ፈርሷል? በአጃቸን ያለው መረኛ እንደሚያመላክተው ያየሁት አይለፈኝ እንደነበርክ ነው። በተሰይ ወደ ስልጣን ከመጣህ በኃላ ብሶበህ ነበር።" ካድሬው ምላሽ ሳይሰጥ አንገቱን አቀርቅሮ ቀረ።

ማሚት ቀዩ ካህሳይን ተቆጣችው። ራሱን በማጋለጡ ሊበረታታ እንደሚገባ አሳወቀች። ወደ ካድሬው እየተመለከተች፣

"ቁልፍ ችግሩ የአሱንና ቤተሰቡን ህይወት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት መምራት አለመቻሉ ነው። ቀድመን ብናገኘው ኖሮ እንታደገው ነበር። የፈሰሰ ውሀ አይታፈስም፤ ከአንግዲህም ቢሆን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባስቀመጠው የችግር መፍቻ አቅጣጫ (ካውንስሊንግና የምክር አገልግሎት) እየተከተለ ቀሪ ህይወቱን መምራት ይኖርበታል። ከመስመር ወጣ የምንለው ይህን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ችግር መፍቻ አቅጣጫ ካልተከተለ ብቻ ይሆናል።"

ካድሬው በማሚት አስተያየት ተበሳጨ። አንሶላ ከተጋፈቶቸ
ብዙዎቹ ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማሸነፍ የወጣትነት እድሜያቸውን የሰ
የህውሀት ተጋዳሊቶች መሆናቸውን ስም አየጠራ አጋለጠ። ይበልጥ ስሜታ
እየሆነ ሲሄድ እንዲህ በማለት የውስጡን ተናገረ፤

"በቅርብ ጊዜ ለህዝብ ይፉ በሆነ መረጃ መሰረት የኤድስ ወረርሽ
ሀገራዊ ስጋት ከፈጠረባቸው ቦታዎች ዋነኛው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ነ
ፌደራል ፓሊስም ተመሳሳይ ነው። በተለይ ከፍተኛ መኮንኖቻችን ከተሰጣች
ኮከብ ጋር ቫይረሱ አብሮ የታደለ እስኪመስል ድረስ አስደንጋጭ ሆኗል። እነ
ባለማዕረግ ታጋዮች ህይወታቸውን የሚመሩት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቾ
ነው።

ካድሬው ስቃይ ስቦ የሚከተለውን ጨኸት ተነፈሰ፤

"...ሌላው ቀርቶ ህመመሙ እየባሰባት ሲሄድ ለማስታመምና ለእረ
እንዲረዳት ከመስሪያድሩ ተዘዋውራ የተከበረው ፓርላማ አባል እንድት
የተደረገችው ተጋዳሊት ካውንስሊንግ የምንወስደው አብረን ነው። የፌደ
ፓሊስ ሁለተኛ ሰው የሆነው ባለቤቷ የምከር አገልግሎት እንዲወስድ ደጋ
ብትጠይቀው ፍቃደኛ አልሆነም። ይህ ቁልፍ የህውሀት ታጋይ ህይወ
በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አቅጣጫ አይመራም ማለት ነው?"

***

የደኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴና የአዲሳባ ምክትል ፕሬዝዳ
የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ደቀመዝሙር ጓድ ካሊድ አብድርሀማን። ኮ
አከሮባተኛ ነበር። በተለምዶ በኢህአዴግ ማምጣጣ ላይ ቀድሞ የተናዘዝ
ለማየት ዝግጁ ነው ተብሎ ስለሚታመን ያለምንም ቅጣት ይታሰ
ለሌሎችም በአርአያ የሚጠቀስ ይሆናል። የካሊድ መገለባበጥ ይህንን
ያደረገ ነበር። ይህ ለዶንቦስኮ አይሰራም። የእነ ካህሳይ፣ ማሚት፣ ሞን
ግዛት።

ማሚት እንዲህ በማለት አውጫጭኙን ጀመረች፤

"ካሊድ ስለትምህርት ደረጃህ ንገረን። ኢህአዴግን ስትቀላቀል
አለኝ ብለህ፣ እኛም የምርጫ መወዳደሪያ ፓስተር ላይ ከፎቶግራፍህ
በፓለቲካል ሳይንስ ዲግሪ ብለን ልደታን በእንተ ፓስተር አጥለቀለቅናት።

ካሊድ ኮስተር ብሎ፤

"የፓርላማ ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው ዶክተር አህመድ
ያታለለኝ። ከካናዳ ስለመጣህ ኢህአዴግና የመዲናይቱ ህዝብ እንደ
ይቆጥርሀል፣ በንግግርህ ውስጥም ጠንካራ እንግሊዘኛና አብዮታዊ
ተጠቀም አለኝ።"

ማሚት ጠረጴዛ እየደበደበች፤

"እትዘባርቅ! የተጠየከው የትምህርት ደረጃህ ስንት ነው? እሱ
መልስ።

"ዲፕሎማ!"

"የምን ዲፕሎማ?"
ካሊድ ሣንቅላቱን እያሻሸ፤
"High School" ብሎ መልስ ሰጠ።
ማሚት ቀጠለች፤
"ነገ አምጥተህ ልታሳየን ትችላለህ?"
ካሊድ እያቅማማ፤
"ዶክመንቶቼን ከካናዳ ገና አልአስመጣሁም። ጊዜ ከተሰጠኝ በቅርብ ጊዜ አስመጣለሁ።"
እነ ማሚት የፓርላማው ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ዶክተር አህመድም ጉዳይ እንዲጣራ ለኢህአዴግ ቢሮ አስተላለፉ። ካሊድ መቼም ብቻውን ሞቶ አያውቅም!!

***

የኢትዮጵያን ፓርላማ ለአስር አመታት የተከታተለ ሰው የእንድ ትልቅ አዛውንት ገፅታ ከፊቱ ላይ አይጠፋም። የፀጉሩ ንፊፈፌ፣ ንብስማንትና አበጣጠሩ የናይጀሪያውን ታዋቂ ፀሀፊ ወሌ ሾይንካም ስለሚመስል የእሱም ቅጽል ስም ይሄ ምሁር ሆኗል። ፀሀፊ ወሌሾይንካም የኖቬል ተሸላሚና የፖለቲካ አቀንቃኝ ነው። ለአፍሪካ ስነ ጽሁፍ እድገት ላበረከተው አስተዋጽኦ የኦዲሳባ ዩንቨርስቲ የክብር ዶክትሬት አበርክቶለታል።

የኖቬል ተሸላሚውን ቅፅል እንደተሰጠው የሚያውቀው የኢኛ ሰው በያንስ በወር አንድ ቀን በፓርላማ ውስጥ ተቋማትን ሲያቋጥጥ ይታያል። ለሸንጐው አባላት አለም አቀፍ ህጐችን፣ የፓርላማ አሰራሮችና ተሞክሮዎችን የእቅም ማንባታ ይሰጣል። ይህ ብርታቱ ከምሁርነቱ ጋር ተደምሮ የማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነ። በተጨማሪም ከፓርላማ እየተወረወረ የአዲሳባን ፓለቲካ ሰራ ድጋፍ እንዲሰጥ ተመደበ... "ዶክተር!" አህመድ።

ይህ ከምእራቡ አለም የመጣ ምሁር የኢህአዴግን ከብር ከፍ አደረገ። ባለሁለት ሰለት ቢላዋ ቢሆንም አንደኛው የዶለዶመ መሆኑን በተግባር አሳየ። ከእነ ዶክተር ካሱ ኢላላ ቀጥሎ ኢህአዴግ አለኝ ከሚላቸው አብዮታዊ ምሁራን ጐራ ውስጥ ተቀላቀለ። ደኢህዴን ደረቷን ነፉች። ኢህአዴግ ደስ አለው። ሁላችንም ከብርና ሞገስ አጐናፀፍነው።

ከእለታት በአንዱ ቀን ለፓርላማው የህግ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ለሆነው አስመላሽ ወልደስላሴ (አባይ ንብሶ) ከዶንቦስኮ መልእክት ደረሰው። አባይ ሰውየውን ጠርቶ እንዲህ ብሎ ጠየቀው፤
"ዶክተር አህመድ የሁሉንም ሰው ዶሴ እያዘጋጀን ስለሆነ ዶክትሬትህን ነገ ይዘህ በአስቸኳይ እንድትመጣ" አለው።
ሰውየው ደነገጠ። ወገቡ ጐበጠ። ታሞም ለጥቂት ቀናት ተኛ። የማይቀር እዳ ነውና አባይ ንብሶ ጋር ቀርቦ እንዲህ በማለት መልስ ሰጠ፤
"አባይ! አባይንብሶዬ! በተለምዶ ሰዎች ዶክተር ስለሚሉኝ ነው እንጂ ዶክትሬት የለኝም።ደግሞስ ዶክተርነት ምን ያደርጋል ብለህ ነው? ዋናው

አብዮታዊነትና የአላማ ጽናት ነው። በዚህ ደግሞ በፊት መስመር በው ድርጅቴን እያገለገልክ ነው።"

አባይነበሰ ሊለቀው አልፈለገም። እንዲህም አለው፣

"እንግዲያውስ አለኝ የምትለውን ዶክመንት ይዘህ ና።"

የተከበሩ አቶ አህመድ አንድ አመት የሰለጠነባትን ሰርተፍኬት ይዞ መጣ...

ኢትዮጵያዊው ወሌሾይንካም!!

ጦላይ ...1990 አ• ም•

ከህውሀትና ብአዴን የተቀነሱ ሴት ተጋዳሊዎችን የቀለም ትግ ለማስተማር ጦላይ ለአንድ አመት ቆይታ አድርጌ ነበር። የጦላይ ህ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመከሰት አድሉ ጠባብ ነው። ጦላይ ርግጥነ ቦታ ነበር...

ከቁመት በላይ በሆነ ስንደዶ ሳር የተሸፈነ፣ ዘንዶና አባብ መሳ የሚርመሰመሱበት፣ አጋዘንና ከርከሮ በር የሚቆረቁርበት፣ ጦጣና ሰው አ የሚሄዱበት፣ ጨረቃ ውበቷን ለማሳየት የሰፈድ ያህል ሰፍታ የምትደግ ቦታ... ጦላይ!

በሐሩር በረሀ ውስጥ አስር ሺህ ሴቶች፣ ከሶስት መቶ የማይ መምህራን የተቆጠጠሩበት፣ አሰቃቂው የደርግና ኢህአዴግ ወታደራዊ ቤት፣ ከደርግ ጀምሮ ሻለቃ ቢራራ የሚል ስያሜ የተሰጠው ምእናባዊ ሪ መንፈስ የነገሰባት... ጦላይ!

ስለ ኢትዮጵያ መስቀለኛ መንገድ ፣አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስጥሙው የማያባሩ፣ ግን ደግሞ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ተጋዳ ያሉበት። በየሳምንቱ በሴቶቹ ቁጥር ኮንደም ጥቅም ላይ የሚውልበት፣ ወንዶች የሚበዙበት፣ ከበሮ ቡጢያለቀ ቁጥር በመቶዎች አቅላቸውን የሚወድቁበት ፣መልአከ ሞት አግጠ የሚታይበት... ጦላይ!

ዘመን የተገለበጠበት ቦታ። ሴት ልጅ ጋብዛና ገንዘብ ከፍላ ተራ ስሜቷን የምታረካበት። ሺዎች ቆመው የሚሸኑበት።

መኃልዬ መኃልዬ ዘጦላይ!!

በዚህ ታሪካዊ ቦታ ከአብሮ አደጌ ከንዑጠር (ስሙ የተቀየረ በአንድ ቤት አንኖር ነበር። ከጐናችን የቅርብ ጓደኞችን የመምህርት ነጻነት የተቀየረ) ቤት ይገኛል። በመኝታ ቤታችን መስኮት ማታ ማታ ያለ "eddie's dead shot in the head for a dollar who going to t mama..."የሚለው ዘፈን ይንቆረቆራል። ከጐረቤታችን መምህርት ነጻነት ነጺ ከለኛ እስከ ሀሙስ ምሽት ያለውን ብቸኝነት ለማባረር ቴፕን እሰ ከፍታ ታጮህለች... ከጦላይ አዲሳባ ጦርሀይሎች ባይሰማም ለእኔና

ነበምስጠር የእንትልፍ ማምጫ ኪኒን ሆኖናል።

ሲዲውን ከነማጫወቻው በማስታወሻ የሰጣት የመከላከያ የትምህርትና ስልጠና መምሪያ ሀላፊው ኮረኔል ነጋሽ ነበር። ሽቅርቅሩ ኮሎኔል አንድ ሰሞን ከአርብ እስከ አሁድ ውሎውን ጦላይ አደርገ። በማሰልጠኛ ጣቢያው የነበሩ ዲሞበላይዝድ ታጋዮች በየጊዜው እንደ ምግብ ሜኑ ይቀርቡለታል። አሁም አልጫን ከቀዩ፣ ምንቸትን ከከትፎ እያማረጠ ይቀረጥፉል። የትግል ጓደኞቹ ባድመና ጾረና ላይ ይረግፉሉ፣ አሱ ሚስቶቻቸውን እንደ ሸሚዝ ይቀያይራል። ይህ ጦላይ ነውና ነውር አይደለም!!

ከቀናቶች በኋላ ተጋዳሊቶች አንባቱ ጋር ደረሱ። በቁት። ፊቱን ወደ መምህራን አዞረ። መምህር ነፃነትን ተዋወቃት። ጦላይ ለሴት መምህራንም ፈታኝ ነበረች። ጠየቃት። ፍቃደኛ ሆነች። ሁሉንም እርግፍ አድርገ ከነፃነት ተጣበቀ። ለምክርና ሀሜት እስኪጋለጥ ድረስ ከንፍ አውጥተው በረሩ። ለጦላይ ከዋኩቡቶች ሆኑ።ከጨረቃዋ ጋር ተጣምረው የምሽት ብርሀን አፈለሱ።

አፈቀራት... ወደደቻው።

ህይወት በዚህ መልኩ ለረጅም ጊዜ ቀጠለ። ይሆን ጣፉጭ ጊዜ ዘለለማዊ ለማድረግ የበረሀ ሚስቱን ፊቶ እንዲያገባት ጥያቄ አቀረበ። "እሮጊድ" ብሎ ከሚጠራት ሚስቱ እንድትገላግለው ተማፀናት።

ነፃነት ማሰላሰያ ጊዜ ጠየቀችው። እኛን አማከረች። ከጊዜያዊ ጥቅምና ሰሜት ወጥታ እንድታስብበት ምክር ቢጤ ለገስናት። ምን ያደርጋል! ማሰላሰያ ጊዜው ሳያልቅ እኔ ጦላይን ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብቼ ወጣሁ። ከምስጠር ተከተለች። አሱ የአንድ ግል ኮሌጅ መምህር ሆኖ ተቀጠረ።

ከእለታት በአንዱ ቀን እንዲህ ሆነ፣

ከንስጠርን ፊልጌ ልደታ የሚገኘው ኮሌጅ ሄድኩኝ። ቅንድቧ ከገጠመ ተማሪው ጋር ሻይ እየጠጣ አገኘሁት። አሰተዋውቆን ጨዋታ ጀመርን። የኢህአዴግ ካድሬ መሆኔን ስታውቅ እንዲህ ብላ ጠየቀችኝ፣

"የአዲሳባ ካቢኔ አባሏን ታጋይ ማሚት ገ/እግዘአብሄር ታውቃታለህ?"

"ታጋይ ማሚት፣ አንዴ እሷን ካላወኩማ ምኑን የአዲሳባ ካድሬ ሆንኩኝ።" አልኳት።

"ወላጅ አናቴ ናት።"

"እድለኛ ነሽ። ጠንካራ አናት አለችሽ።"

"ኧረ ባክህ፣ ብዙ ሰው እንደዛ ይለኛል። በተለይ ስራውን በአግባቡ የማይሰራ፣ ቤተሰቦቹን የማያከብር፣ የሚማማጥ ሰው አትወድም ሲሉ ሰምቻለሁ። ለነገሩ እቤት ውስጥም ሲርየስ ናት!"

"ምን ትነግሪኛለሽ? ዶንቦስኮ በሚባለው የካድሬ ማሰልጠኛ እንዴት እንደምታንቀጠቅጥ አውቃለሁ።" አልኳት።

ከንስጠር በእራ ውስጥ ይዞት የነበረው ሻይ በትንታ ተደፋ። ልጅት መናገሯን ቀጠለች፣

"አባቴንም ታውቀው ይሆናል የመከላከያ ስልጠና ክፍል ሀላፊ ነው ኮረኔል ነጋሽ ይባላል።"

አፈጠጥኩባት...ደነገጥች። እኔም ከድንጋጤ ሳልወጣ፣

"መጀመሪያ ገጽታሽን ሳየው አዲስ አልሆነብኝም። የአባትሽ ግልባጭ ነሽ "አልኳት። ርግጥም የልጅቷ መልክ ቁርጥ አባቷን ነው። የእጅና እግሮቿን ፀጉ ጨምሮ። አፍታም ሳይቆይ ጠላይ ከሀመሳ አስከ አርብ የማየው ጥቁ ላንድክሩዘር ኮሌጁ በር ላይ ቆመ። የኮረኔል ነጋሽ ሹፌር ከርቀት አየሁት...

ተሰናበትን ሄደች።

ከንቡጠር ሳቁን ማቆም አልቻለም። በግርምት ውስጥ ሆኖ ኮረነ እንደ ካልሲ የቀያየራቸውን ተጋዳሊቶች ጣቶቹን እያነሳ መቁጠር ጀመረ ትርሀስ፣ አባዲ፣ አልማዝ፣ አብርሽት፣ አልጋነሽ ፣ማርታ፣ ትበርህ፣ ዘርፊ የእጁቹ ጣቶች አለቁ። እኔንም ወደ ኃላ ጐተተኝ። በፉንታዬ ወደ ዶንቢ በመሻገር በማሚት ምህረት የለሽ ሰይፍ የተቀሉትን መጥራት ጀመርነ ንግስቲ፣ አልማዝ፣ ጣይቱ፣ ካሊድ፣ አበበ ዘልኡል... ኧረ ቤቱ ይቁጠረው።

(ፊት ለፊታችን የተጋረጡ ሀገራዊ ጉዳዮች እንስተን ሰንፈርስ የዲ ተድባበ ጥላሁን ካዛንችስ መስታወት ግልባጮች ስለነበሩ ሁለት ታሪ ቢታዎች አናወጋለን። ዝዋይ ሀዛናት አምባና ጠላይ ካምፕ። በዝዋይ ሀ አምባ የዛፈዎቹን ጀንራሎች ፍስሀ ማንጁስ፣ ወዲ መድሀን፣ ወዲ ኩ ለማስልጠን ቆይታ አድርጌ ነበር። በኢህአዴግ መከንኖችና በባላንጣዎቻ የመንጌ ልጅች መካከል የነበረው መገታተር አሳዛኝ ነበር። በተለይ ለአ አዳም በደረሱ እንስቶችና በገንዘብና ንልበት ሊገዟቸው በሚዳከሩት ባለሟ ወታደሮች መካከል የነበረው ትግል ከሀሊና የሚጠፋ አይደለም። ከመኮ ሚስቶች ጋር ደግሞ በጠላይ ... መጎልዬ መጎልዬ ዘጠላይ!)

***

የሞንጆሪኖ ልቅሶ...

በሰፈሩት ቁና ሆነና ነገሩ የህውሀት መስንጠቅ የሞንጆሪኖን ፍጻ አገዛዝ እንዲያከትም አደረገዉ። በእርግጥ የተስፈግርያምን የህል ወ ከማርዬስ አልደረሰባትም። ከአቶ መለስ ተግሳፅ ውጭ።

አቶ መለስ እንዲህ አላት፣

"ሞንጆሪኖ አዲሳባን የለውጥ ማዕበል ውስጥ አስገብተሽ ታስተካከ ብለን ነበር የላክንሽ።እንቺ ግን የድርጅቱን አደራ በልተሽ ከጅርባ ሰታ ከረመሽ። ኧረ ለመሆኑ ምን ጉድሎበሽ ነው? እነ ስዬን ሳታዉቂያቸው ነው፣ አብረሽ ድርጅቱ ላይ ገመድ ልታጠልቂ የነበረው?"

ሞንጆሪኖ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። ስጋ ሰውአትን ጠርታ ሀ እንደማይለመዳት ቃል ገባች። እግሩ ላይ ተደፍታ ይቅርታ ጠ

ወልዩ ጋር እንዴት እንደተመሳጠረች ዘከዘከች። የህቡዕ እንቅስቃሴው ስት ወር በፊት በአዲሳባ መጀመሩን አስረዳች። በአዲሳባ ያሉት የዞን ሊቀ ዘት ትልቁ ስራቸው ይህ መሆኑን ገለፀች። ካድሬዎቹ አባዝተው ኮኑት ወረቀት ዘከዘከች። አመናት።

ፊቱን ወደ እሷ አነሳ...ራራላት።

.

እንደ ቀድሞ ባሏ አባይ ፀሀዬ የምህረቱ ተቋዳሽ አደረጋት። የዘመናዊ ት ማነስ የፈጠረው ችግር ሊሆን እንደሚችል በመግለፅ፣ የቀለም ርት እንድትማር ፈረንጅ ሀገር ሰደዳት። ትምህርቷን አጠናቃ እንደመጣች ጠቅልላ መቀሌ ገባች። የትግራይን ካቢኔ ተቀላቀለች። ለእቶ መለስ ያላትን ነቷን በተግባር አሳየች፣ እሱም ካሳውን በቁመ ተቀበለ። በዚህ ሳይወሰን ሀት ሁለተኛ ትውልድ ውስጥ እንድትታቀፍ የመጀመሪያው ምርጫ ንት!

***

(የአቶ መለስ ግብአተ መሬት ከተጠናቀቀ በኃላ ሐልፎ ሐልፎ ኢቲቪ ከታለሁ... ታዲያ አንድ ምሽት ቲቪውን ወደ ቻናል 280 ሳዞረው ዮጵያ ፓርላማ አየቀረበ ነበር*** የፓርላማ አባላቱ ለአንድ ሚኒስቴር ት ጥያቄ ያቀርባሉ። ከሀዘብ የተሰበሰቡ ጥያቄዎችን አንድታቀርብ ዊት የፓርላማ አባል አደል ተሰጠ። ከብርት የፓርላማ አባሏ መናገር ቻች። የሴትየዋን ድምፅ አውቀዋለሁ። ካሜራው ቀጥሎ ስሟን አሳየ፡ ትለወርቅ"** አላውቃትም። ቀስ በቀስ ምስሏን ሲያሳይ ሴትየዋ ምንጅሪኖ ለካስ ምንጅሪኖ ፈትለወርቅ ሆናለች።... የአዲሷ ፈትለ ወጣትነት የድሮዋ ሪኖ ነው። አፍታም ሳይቆይ የህውሃት ድርጅታዊ ጉባኤ በመቐለ ተካሒዶ፣ ወርቅ የህዉሃት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆነች።)

***

ምእራፍ ስድስት

ኢህአዴግን ከአዲሳባ ያባረረው - ምርጫ 92

"እናንተ እኮ ጅሮ ስለሌላቸሁ ነው። የአዲሳለባ ህዝብ አንቅሮ ተፍቷችኃል። የተተፋ ደግሞ ተመልሶ አይዋጥም።"

ከንፈ ሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ)

የተዳፈነ ታሪክ!

ብዙዎች የአዲሳባ ህዝብ ምርጫ ካርድ በምትባል ሰላማዊ ኢህአዴግን የቀጣው በምርጫ 97 አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ የተሳሳተ ኢህአዴግ ላይ የመዲናይቱ ህዝብ የወሰነው በሁለተኛው አገር አቀፍ 1992 ዓ.ም ነበር። በዚህ ምርጫ ኢህአዴግ አሳፋሪ ሽንፈት ተከናንቧረ ብዙ ያልተነገለት ታሪክ በወቅቱ መሪ ተዋንያን በነበርን ካድሬዎች ዘንድ ዳር ጨዋታ ሆኖ ሰንበቷል... በእንደዚህ መልኩ ለንባብ አስኪበቃ ድረስ

በምርጫ 92 ኢህአዴግ መሸነፉን አስቀድሞ ካረጋገጠ የተከተለው ስትራቴጂ የህዝቡን ወሳኔ ባይቀይረውም ለማግ ጠቅሞታል። በምርጫው ማግስትም የህዝቡን ተቃውሞ ለማስቀየስ አገር አቀፍ እጅንዳዎች ተቀርፀው ተግባር ላይ መዋላቸው ጉዳዩ እን አድርጎታል። የሄጉ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ባድመ ላይ የሰጠው ተከትሎ "የጦርነቱ ድል በፍርድ ቤት ተደገመ" የሚል የተሳሳተ በመስጠት የመዲናይቱን ህዝብ መስቀል አደባባይ እንዲወጣ የ በምርጫው ሳምንት ነበር።

በጨፌ ግምገማ ኢህአዴግ በመሸነፉ ላይ ጥያቄ አንስቶ የ አልነበረም። ይልቁንስ ሽንፈቱን የሚያሳዩ ሰፋፊ መገለጫዎች ቀረቡ። መቀልበስ ተከትሎ በመዲናይቱ ተከስቶ የነበረው አመፅና ነውጥ ባይቀጭ ሊከሰት የነበረው አደጋ በሰፊው ተነገረ። በተሰፋ አስትና ችጋር የተመታው ነዋሪ አደራጅቶ የሚያነቀሳቅስ ተቃዋሚ ቢኖር እንደዚህ ተቀምጦ ስለአዲሳባ የምንነጋገርበት ሁኔታ እንደማይፈጠር ምርጫውን ለመቀልበስ በተግባር የዋለው ፀረ ዲሞክራሲ ቢሆንም አ ዲሞክራሲን እንደታደገው አስተያየቶች ቀረቡ።

በተለይም የደህንነቱ ሹም ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ፣

"የታደግናችሁ እኛ ነበርን" ብሎ በኩራት ሲደሰኩር መስማት አስገራሚ ነበር። በእያንዳንዱ ወረዳ በአሱ ፈትአውራሪነት የተሰራውን ሸፍጥ በዝርዝር ማቅረቡ አስገመተው። እንደ እውነቱ ከሆነ ከእንድ የደህንነት ባለስልጣን ያሚጠበቅ አልነበረም። ምንም እንኳን ሀቁ አሱ የተናገረው ቢሆንም።

ኢህአዴግ በሁለተኛው አገር አቀፍ ምርጫ በአዲሳባ ክልል ም/ቤትና የፓርላማ ተወካዮች እንደሚሸነፍ ያረጋገጠው አስቀድሞ ነበር። በወቅቱ የቅንጅት ዳሰሳ ጥናት እንዲሰራ የታዘዘው ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል ኢህአዴግ ችግር እንደሚያጋጥመው ሲፈራ ሲቸር አቀረበ። በከቡር ገና ሲመራ የነበረው የአዲሳባ ንግድ ም/ቤት በበኩሉ እንደ ዋልታም ባይሆን የተቃዋሚ አጩዎች በሰፊው ም/ቤት እንደሚገቡ አመላከተ።

ይህንን ተከትሎ ኢህአዴግ የምርጫውን ዲሞክራሲያዊነት የሚያጠፉ ሶስት አርስ በራስ የሚመጋገቡ ስትራቴጂዎች ነደፈ። እስትራቴጂዎቹ እንደሚከተለው ነበሩ፣

በአጩ ምዝገባ ወቅት በተቃዋሚ ፓርቲ አጩዎች ውስጥ ለኢህአዴግ የሚሰራ አሰርጉ ማስገባት፣ በየወረዳው ምርጫ ቦርድ በሚፈቅደው መሰረት የተፎካካሪ አጩዎችን ብዛት አስከመጨረሻው መለጠጥ፣ እና በምርጫው የመጨረሻ ቀናት የተቃዋሚ ፓርቲ አጩዎችን ከተቻለ በማሳመን ካልተቻለ በመደለልና በማስገደድ ራሳቸውን እንዲያገሉ ማድረግ የሚሉ ነበሩ።

በጨፌው ግምገማ ምርጫ 92 ሙሉ ቀን ፊጅዮ ባለመጠናቀቁ ሰበነጋታው ጠዋት ቀጠሮ ተያዘለት። እንደተለመደው ከፍስሀ ጋር ተያይዘን ወደ ራስ ሆቴል ሄድን። እውነት እውነቱን ለመነጋገር። ትኩረታችንም ምርጫ 92 ሆነ። አድማሳችን ደግሞ እኔ እና አሱ ከመራነው ዞን ሁለት የሚነሳ ሆኖ መላ አዲሳባን የሚያዳርስ። ተጨባጭ መግለጫዎችን አንስተን የኢህአዴግን ሸንፈት አረጋገጥን።

በወቅቱ ከመስቀል አደባባይ - አየር ጤና፣ ከፈጥኖ ደራሽ ላፍቶ የተዘረጋውን ዞን ለመከታተል አራት የዞኑ ካድሬዎች፣ ከካዛንችስ ደግሞ ፍስሀ መአሲ ተመደብን ነበር። በዞኑ ውስጥ ያሉ ወረዳዎችን (ወረዳ 20፣21/22፣23፣ 24) እንድንከፋፈል ተደረገ። ምርጫው ተጠናቆ ሲመጣ የአራቱም ወረዳ ውጤቶች ለየቅል ሆኑ።

አስቲ አያንዳንዱን ወረዳ እያነሳን በዝርዝር ወደ መመልከት

እንሸጋገር።

***

ፍስሀ መአሲ ወረዳ 23 (ሳፍቶ ከ/ከተማ) ለመምራት ሳርቤት ከ
በእሱ ፊትአውራሪነት በወረዳ 23 ኢህአዴግ ያስቀመጠው የመጀ
እስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ ተፈፀመ። መምህር ዳኞ የሚባል የባስሊዎስ ኦ
ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መኢአድን ወክሎ ለመወዳደር ፍ
ሆነ። አሸንፎም ወደ ምክርቤት ገባ። በወሰደው ኦረንቴሽን መሰረት የተሰ
ተልእኮ በእግባቡ አከናወነ።

የምክር ቤት ስብሰባ ከመካሔዱ ሶስት ቀን አስቀድሞ መኢአድን
የሚናገረው መምህር አንተነህ ምን እንደሚያቀርብ ሪፓርት በዳኞ
ይደርሰናል። እኛም አስቀድመን ምላሽ በማዘጋጀትና ማን ምን እንደ
በመከፋፈል ሰውየውንና መኢአድን እንቀጠቅጣለን።

ፍስሀ ረታ የሚባል የአካባቢው ተወላጅ ወጣት እንዳ
ከማድረግና መምህር ዳኞን አሰርገሎ ከማስገባት ውጭ በሌላው አልተሳካ
በወረዳው የተወዳደሩት (የካቢኔ አባልና የኢኮኖሚ ዘርፍ ሀላፊ የ
ዶፌቅን) ጨምሮ ሁሉም በዝረራ ተሸነፉ።

***

እኔና የዞን ደህንነት ሀላፊው የትውልድ ቦታዬ ወደ ሆነው ወ
ከልፊ ቀራንዮ ሄድን። ኢህአዴግ ያስቀመጠውን ሁለተኛና ሶስተኛ እ
መተግበር ጀመርን። ፓርላማን በተመለከተ ምርጫ ቦርድ በሚፈቅደው
የተፎካካሪ እጩዎችን እስከመጨረሻ መለጠጥ ሲሆን፣ ከልል ም
በተመለከተ የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ከምርጫው ራሳቸውን እ
ማድረግ የሚሉት ነበሩ።

ለፓርላማ መቀመጫ የሚፎካከሩ እጩዎችን ምዝገባው ሰ
አንድ ቀን ሲቀረው ከ6 ወደ 12 አሳደግን። በተለይም ኢህአዴግ ሙሰ
ይሸነፍባቸዋል ብለን በለየናቸው አካባቢዎች በቀበሌያቸው ሃ
ያላቸውን ግለሰቦች ለየን። የግል እጩዎች ሆነው እንዲወዳደሩ አግባ
ፍቃደኛ የሆኑትን ፒትሽን አባሎቻችንን በማስፈረም ለምርጫ
አስረከብን። ፓርላማና ከልል ምክርቤት ተመርጠው ሲገቡ የሚያገኙ
እጋኑን አሳየናቸው።የስልጣን ተስፈኞች ሆኑ።

በወረዳ 24 ለፓርላማ የቀረቡት የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ከአ

አበበ ቀስቶ ገራሚ ሰው ነው። በካድሬነት ዘመኔ ኢህአዴግን የሚንቅ አጋጥሞኝ አያውቅም። ብዙሀኑ በፍራቻ አቅማዳ ውስጥ ተደብቆ ነው ለእት ኢህአዴግን በአደባባይ በመቃወም፣ ሌቦችን በማጋለጥ ፋና ወጊ ስለብዙዎቹ ባለስልጣን የማያውቀው ሚስጥር የለም። በምርጫ 92 ኋኋ መስመር ብንሰለፍም መቀራረብ ፈጥረን ነበር። ብዙ ነገሮችን ቆኛል። በሂደት ሳጣራው የተጋነኑ ነገሮች ቢኖሩም አብዛኛቹ ትክክል

በተለይ የህዝቡን ስሜት ከማንበብ አንጻር ከፍተኛ ብቃት ነበረው። ችን በቁጥር እየጠራ፣ "በዚህ ታሽንቆኛላችሁ፣ በእነዚህ ደማሞ በገረራ ለሁ" ይለን ነበር። እያደር የአበበ አሸናፊነት ፍንትው ብሎ ወጣ። ጫው ፉከክር ገለል የሚልበት አማራጮች ታሰቡ። አሱን ማስፈራራት ለብ አልነበረም። ምድር ቢንቀጠቀጥ የማፈራ ሰው አይደለም። በቁጥጥር ማዋል ደግሞ ወንጀል ሲሰራ አድ ከፍንጅ መያዝ አለበት።ስለዚህ የቀረው ሌረሻ አማራጭ በገንዘብ መደለል ሆነ።

ለመደለያ የሚሆን ገንዘብ ማግኘት አስቸጋሪ አልነበረም። ድብቅ አላማ ፓርላማ መግባት የሹመጠው ዶክተር ቶፊቅ አጠገባችን አለ። የዶክተሩ ጅ መሠ የሚያወጣውን ግራው እያውቀውም። እናም ለአበበ ቀስቶ ሀምሳ በር መደበለት። አግቡበተው እንዲሰጡት ደግሞ ጓደኞሞቹ ዳኛ ልዑል ያምና ኪሮስ ተመራጭ ሆኑ። ዳኛ ልኡል በአካባቢው የሚኖር ሲሆን ሌው ካድሬዎች ልዩ አማካሪ ነበር። ይህ የህውሀት አባል የሆነ ዳኛ አዴግ ከፍተኛ አመኔታ የሚጣልበትና ትላልቅ ፓለቲካ ቀመስ የፍርድ ቤት ችን የሚመለከት ነው። ኪሮስ ደግሞ የቀበሌው የበላይ ጠባቂ ነው። ይህ የጎሳነው የቀበሌ ንጉስ በወረዳው ካድሬዎች ዘንድ "ኪሮስ አይናማው" ል ይታወቃል። በወረዳውና በቀበሌ ዘ ውስጥ የፈለገውን እንዲያደርግ ዶለታል። ኪሮስ ምንም አይነት ድርጅታዊና መንግስታዊ ስልጣንና ስራ ረውም የካዘንችሁ መንግስት እለቃ የነበረውን ተስፉማርያም በየጊዜው ፣ መረጃ ያቀብላል። የወረዳ አመራሮችን በተናጠል እየጠራ የስራ ቱሸን ይሰጣል። ያስፈራራል።

ዳኛልዑልና ኪሮስ አይናማው ገንዘቡን ከዶክተሩ በመቀበል ማግባባቱን ኑ። በቀበሌያቸው መገናኛ ከበብ አብረውት መታየት ጀመሩ። እያደር ዘአዴግ ምርጫ ኮሚቴ ተስፉ ሰጪ መልእክቶች መሰማት ቀጠሉ። አበበ ላይ የሚደረገው የእግር ለእግር ከትትል እንዲቋረጥ ተደረገ።

ምርጫው ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀረው አበበ ቀስቶ ውሳኔውን ህ በማለት አሳወቀ፤

"...የተጋበዝኩትና ብራችሁን የተጠቀምኩት እናንተ ጋር የማይነጥፍ ማምረቻ ስላለ ነው። ምርጫ የምወዳደረው ግን ለገንዘብ ሳይሆን ይህን ፊ ስርአት ለመጣልና ለነፃነቴ ነው።በዚህ ላይ ለመደራደር ህሊናዬ

የኢህአዴግ አፍ ሆኖ የቀረበው።

አንድ አሁድ ዶክተሩንና ሌሎች የክልል ምክርቤት አፀውፎ ለማስተዋወቅ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 (አየር ጤና) አዳራሽ የህዝብ ስብሰባ ጠራ አንዲት ሴት አንባዋን እየዘራች ዶሩ ለከፉ ቀን ያስቀመጠችውን ወርቅ ማሸ ሳይበቃ የኤድስ ቫይረስ ሳይኖርባት አለብሽ እንዳላት አጋለጠች። እሱ የሰጣ የምርመራ ወጤትና ሌላ ከሊኒክ ተመርምራ ነፃ የሆነችበትን ወረቀት አሳየች።

በቀጠለው ሳምንት በቀበሌ 09 (ፊጥኖ ደራሽ) አዳራሽ በጠራ ስብሰባ ሌላ ሴት ከባለቤቷ ጋር መጥታ ተመሳሳይ ነገር አቀረበች።አንዳታች ደቃን።መረጃውን ለካዛንችስ ስውሩ መንግስት ብናቀርብም የድርጅቱ ህል ይቀድማል በመባል ውድቅ ተደረገ።

አቶ በረከት ስምኦን በሁለት ምርጫ ወግ መፅሀፉ በገፅ 126 ላይ ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይ ህዝቡን ያከብራል፣ ይፈራልም። ሁ እንደሚለው ከህዝብ ውጭ ሌላ ጌታ የለውም ይላል፣

በዚህ የስምኦን ልጅ አባባል ግልባጭ ስሌት መሰረት ደ/ር አምስት አመት ያልመረጠውን ህዝብ ወክሎ በፓርላማ ተቀመጠ።ቀጣ በየመን የኢትዮጵያ ባለ ሙሉ አምባሳደር ሆኖ በመሾም ለአምስት አ አገለገለ።በየመን የጀመራትን ስራ ከግብ አድርሶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ደግሞ "የግጭት አፈታትና ምናምንቴ..." የሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድ አቋቁሞ የሪፓርተር ጋዜጣ የዘውትር እንግዳ ሆኗል። ከዛም አልፎ ሁላ ቤት አንኳኩቶ ለመግባት ለትልቅ ቦታ ራሱን አጩ አድርጐ ቀርበ ዶክተሮቻችን የሚሯሯጡበት ቦታ።

ይህቺን ቦታ የካፊኦ ልጅች" አሻሮ ይዘህ ወደ ቆሎ የምትጠ ይሏታል። የሀገራቸው ልጅ ዶክተር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ አባባሉን ወደ ከለወጡት ሰዎች በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። የካፊኦ ልጅች ጊዘ ሲደርስ በሌላ ማስታወሻ የዶክተር አሸብር የህበት ማማ ምንጩን ይነግ ለአሁኑ ተረኛው ዶክተር ቶፊቅ አብድላሂ ነው። የሀረሬን ክልል የኢትዮጵያ ስፓርት ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ለመሆን እጩ ተወዳዳሪ ሀ በሎ ነበር። ለጊዜው ግማሽ ቢደርስም አልተሳካም። የዛፉው መከ መደላድል ለመፍጠር እንደሆነ ይታመናል። ማን ያውቃል ለዚህ ዱረሽ በሎ የሚያመሰግነው አምባሳደር ግርማ ብሩ "የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ" ሆኖ አዲሳባ በመምጣት ህልሙን ያሳካለት ይሆናል።

***

ይህ ደግሞ የከንፈ ሚካኤል ታሪክ ነው... አበበ ቀስዮ።

በአጠቃላይ መልኩ የወረዳ 24 ህዝብ ለአዲሳአባ ከልል ምክርቤት
፣ ሚፍታህ አብዶ መርጦ የተቀሩትን አራት ወንበሮች ለመኢአድና
ኣፓ ሰጠ። እኔና ሚፍታህ የተመረጥነው ህዝቡ ስለፈለገን አይደለም።
ዳው ደህንነት ሀላፊ (ዘካርያስ ይባላል) የተቃዋሚ እጩዎችን አስፈራርቶ
ይመዘገቡ ስላደረገ ነበር። በርግጥ ከኢህአዴግ እጩዎች አብላጫ ድምጽ
ው በአካባቢው ተወልደን በማደጋችንና ነዋሪው "ላም አሳት ወለደች..."
ት ነበር።

ህዝቡ ኢህአዴግ ላይ የመረረ ጥላቻ እንዳለው ለማየት የተቃዋሚ
ጅዎች እና ኢህአዴግ ያቀረባቸውን እጩዎች ፕሮፋይል ከምርጫው ውጤት
ማገናዘብ በቂ ይሆናል። ኢህአዴግ ለአዲሳአባ ከልል ምክርቤት ሁለት
ሚስቶች፣ ሁለት የሒሳብ ሙያተኞች፣ አንድ ኤሌክትሪካል ኢንጂነር፣
ዶክተር አቀረበ። ኢዴአፓ ሁለት ከፖኛ ከፍል ያልዘለሉ ትንቢተ
ኢያስ የሚባል እንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጥበቃ ሰራተኞች አቀረበ።
ኣድ በበኩሉ ስራ አጥ የነበሩና የአካባቢያቸው ማህበረሰብ በደባል ሱሰ
ነውቃቸውን እርቁ አድርገው አቀረበ። በመሆኑም ከግለሰብ አቅምና ስብእና
ጋ ልዩነቱ የሰማይና የምድር ይህል ነበር። ነዋሪው ግን ዶክተሩም፣
ሚስቱም፣ ኢንጅነሩም፣ አካውንታንቱም ባፍንጫዬ ይውጣ ብሎ
ኢዴግ ግልፅ መልእክት አስተላለፈ።

***

ጨዋታችን የፔንዱለም ጉዞ ነውና ጉድና ጅራት ወደተባለው
ተሩና አበበ ቀስቶ ወግ እንሸጋገር።

እንዲህ ነበር የሆነው።

የእጩ ምዝገባ ከተጠናቀቀና መቀየር የማይቻልበት ደረጃ በደረሰበት
፡ በዶክተር ቶፊቅ አብድላሒ ላይ መረጃዎች መጥረፍ ጀመሩ። በየመድረኩ
ርብበት ተጨባጭ ኢንፎርሜሽኖች ጆሮ የሚያተሉ ሆኑ። በከፍተኛ
ል የሚያስጠይቁት አስከመሆን ደረሱ። ዶክተሩ በቴዎድሮስ አደባባይ
ቢ ከፍተኛ ከሊኒክ ነበረው። በወቅቱ ለሴት አህቶቻችን የድህነት
ላጪ መንገድ ተደርጐ የተወሰደው ወደ አረብ ሀገር መሄድ ነበር። ዶክተሩ
በመጣንዙብ ወደ አረብ ሀገር በተለይም ወኪል ጽ/ቤት አለኝ ብሎ
ናገረው የመን ሀገር በቀላሉ እንደሚልክ ያስታውቃል። የአጠቃላይ
ና ምርመራ ኤድስን ጨምሮ ከአያንዳንዷ ሴት ከአንድ ሺህ ብር በላይ
ላል። ከአምስት መቶ በላይ አህቶቻችን የተጠየቁትን ከፍለው
ፆራውን በመውሰድ ጉዞአቸውን ይጠባበቃሉ። ተስፋቸው ሲሟጠጥ ቅሬታ
ማሰማት ይሸጋገራሉ። ሁኔታው በዚህ ደረጃ እንዳለ ነበር ዶክተሩ

የኢህአዴግ ሁለተኛ መከራከሪያ በአለማችን የዲሞክራሲያዊ ግንባ ቁንጮ ላይ የተቀመጡት እነ እንግሊዝና አሜሪካ የሚጠቀሙት የአብላ ስርአት እንደሆነ በመግለፅ የዲሞክራሲያዊነቱን መተማመኛ እማኝ እንደ ማሳየት ነው። የኮረጅነው ከእነዚህ ሀገሮች ነው በማለት።

አቶ በረከትና ኢህአዴግ ይህንን አመክንዮ ሲያቀርቡ እንድም ከጀርባ በታኮነት ያስቀመጡትን በምርጫ ጣቢያዎች የሚወዳደሩ አጨም ብዛት የሚያሳየውን የምርጫ ህግ አይጠቅሱም። ከዚህ በተጨማሪ በእንግሊዝና አሜሪካ የአብላጫ ድምፅ ስርአት ዲሞክራሲያዊ የሆነ ምክንያት ስንት ፓርቲዎችና ግለሰቦች እረስ በራስ እንደሚፎካከሩ ለመመ አልፈለጉም። በአሜሪካን ሀገር ከሞላ ጎደል የሁለት ፓርቲ ስርአት የተ ሲሆን በምርጫ ወሳኝ ተፎካካሪ ሆነው የሚቀርቡት የሁለቱ ፓርቲ አጨዎች ናቸው። በእንግሊዝም ቢሆን የመድብለ ስርአት ቢዘረጋም በምር ብርቱ ተፎካካሪ የሚሆኑት ከሶስት ፓለቲካ ፓርቲዎች አይበልጡም።

የኢህአዴግ የአብላጫ ስርአት ከምርጫ ህጉ ጋር በመመጋገብ በህ ያልተመረጠን ኃይል እንዴት ወደ ስልጣን እንደሚያመጣ ከብዙሀን የያ ስርአት ጋር በማወዳደር ማየት ይቻላል። ለማሳያ እንዲሆን የወረዳ 24 ም ውጤት ማየቱ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል።

የብዙሀን ድጋፍ ስርአት ምን ይላል?

ከዲሞክራሲያዊ የምርጫ ስርአቶች አንዱ የሆነው የብዙሀን ስርአት የሚመራበት መርህ በአንድ የምርጫ መወዳደሪያ ክልል ውስጥ አ ሆኖ የሚመረጠው ከሀምሳ በሙቶ በላይ የሆነውን የህዝብ ድምፅ ያገኘ ነው። አንድ ተፎካካሪ ከሀምሳ በሙቶ የድምፅ ብልጫ ካላገኘ ሁለተኛ ምርጫ ይካሄዳል። በሁለተኛው ዙር በተወዳዳሪነት እንዲቀርቡ የሚደ በመጀመሪያው ዙር በድምፅ ብልጫ አንደኛና ሁለተኛ የወጡትን ተወዳዳ ይሆናል። ይህ የምርጫ ስርአት አብዛኛውን የህዝብ ድጋፍ ያገኘ አንዲ ስለሚያደርግ ተቀባይነት ያለው መንግስት ለመመስረት ያስችላል።

የኢህአዴግ የምርጫ ስርአት የብዙሀን ድጋፍ የሚከተል ቢሆ በ92 ምርጫ በወረዳ 24 የሁለተኛ ዙር ተፎካካሪ ሆነው የሚቀርቡት ኦ ዶፊቅና አበበ ቀስቶ ይሆኑ ነበር። ምርጫው አስር ጊዜ ቢመለሰ የአበበ ቀስቶ አሸናፊነት ሳይታለም የተፈታ ይሆን ነበር።

ቦው እና የራሳቸው ደጋፊ ያላቸው መሆኑ በተጨማሪነት ጠቅመን።
ን ወክሎ የቀረበው ከንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) በወጣቶች፣ከፍሌ
(የቅንጅት አመራር የነበረ) በምሁራንና ነጋዴው ማህበረሰብ፣ የትግሬ
ው ሀጂ መሀመድ በሙስሊም ዘንድ ተቀባይነት ነበራቸው። የሰርቶ አደር
አዘጋጅ የነበረው ታዲዮስ ታንቱ በቀድሞ ስርአት ደጋፊዎችና መታደሮች
አግኝቷል። ሌሎቹ 7 የግል ተወዳዳሪ እጩዎች በእኛ የቀረቡ ሲሆን
ግን መምረጥ በማይፈልገው አካባቢ ድምፅ እንዲሻሙ የተዘጋጁ
። ኢህአዴግ በእጩነት ዶ/ር ቶፊቅ አብድላሒን አቀረበ። ለዶክተሩ እጩ
ታላቢ የተደረገው የእስልምና እምነት ተከታይ መሆኑና የግል የህክምና
ባለቤት ስለሆነ ታዋቂነት አትርፏል በሚል ነበር ...
ጉድና ጅራት ከወደኃላ ቢሆንም!

ምርጫ ተጠናቆ ቆጠራው ሲካሄድ የኢህአዴግ እጩ 16%፣ አበበ ቀስቶ
ፍሌ ጥግህ 7%፣ ታደዮስ ታንቱ 6 % አገኙ። በመሆኑም በአብላጫ
: አሰራር መሰረት ከ84% በላይ ህዝብ ያልመረጠው የኢህአዴግ እጩ
ፓርላማ ገባ። ከውጤቱ ማየት እንደሚቻለው አግባብተን ካስገባናቸው
እጩዎች አንዱ ራሱን ቢያገል ውጤቱ ግልብጥብጡ ይወጣ ነበር፣
ኤግን የወከለው ሰው ፓርላማ አይገባም ነበር።

የዶክተር ቶፊቅን አሸናፊነት ያረጋጠት የዜሮ ድምር መጫወቻዎቹ
ሠንሰስት እንቀፅ 54 እና የተፎካካሪ እጩዎችን ብዛት ወደ አስራ ሁለት
ው የምርጫ ህግ አርስ በራስ ተገራርሰው ነበር። የህገ መንግስቱ አንቀፅ
4) የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች
ዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆንበትን
ን ይዘረጋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ኢህአዴግ ጨፍኑና ላሞኛችሁ አይነት
ራክሪያ ጭብጦችን ስለሚያቀርብ ሁኔታውን ገለጥለጥ አድርገ ማየት
ነጊ ይሆናል።

ኢህአዴግ በመጀመሪያ የሚያቀርበው መከራከሪያ ይህ የህገ-መንግስት
ነ በዲሞክራሲያዊ ሰርአቶች ከሚታወቁት የምርጫ ስርአቶች አንዱ
ውን የአብላጫ ድምፅ መጠቀሙን እንደሚያመላክት ነው። ርግጥም
ው እንደሚለው በዲሞክራሲ ግንባታ አስከ አሁን የሚታወቁት የምርጫ
ቦች የብዙሀን ድጋፍ፣ የተመጣጠነ ውክልና እና የአብላጫ ድምፅ ሲሆኑ
ዴግ የሚጠቀመው በመጨረሻ የቀረበውን ነው። ይህ የምርጫ ስርአት
ዳዳሪዎች መካከል አብላጫውን ድምፅ ያገኘ አሸናፊ የሚሆንበት ሲሆን
ረቱ ዲሞክራሲያዊ ገፅታ ያለውና ምርጫውን ለማስፈፀም ቀላልና ወጪ
ጊ ነው።

ጠንቅቆ ያውቃል። በነካ እጁ የፖሊሲውን ባለቤት "ግራኝ መሀመድ" ቢለዉ የጅግንነት ካባ አናለብሰው ነበር።

የሴትየዋ የለቅሶ ምንጭ ከቁጥጥሯ ውጭ በሆነ ነገር እንደሆነ ቆይ የተገለፀለት እግዜሩ፣ "...ገነት እኔ ያልኩት ጊዜ ሰጥተሽ ከእኛ ጋር እንደ እሬ ተንቀሳቀሽ ነው" ብሎ አለዘባት። ወርቃአበባ የምትባል የዞን ካድሬ አብሪ እንድትዞር መደበላት።

ከብርቷ የትምህርት ሚኒስቴር ስራዋን ትታ ወረዳ 21/22 ሰነበተ አግሯ እስኪላጥ ተንከራተተች። በመንደር ውሻ እስከመነከስ ደረሰች።

ምርጫው ሳምንት ሲቀር ባለችው አሁድ አመሻሽ ላይ ሚኒስት ወርቃአበባ ለሳምንታዊ ግምገማ ዞን መጡ። ካድሬዎች እስኪሰባሰቡ ድረስ ቢሮ አረፍ አሉ። የሚኒስትሯ አይን ከወትሮው በተለየ እንደ ስጋ ቤት አን አብርቷል። ከጫት ላይ ተነስታ የመጣች ትመስላለች...ወርቅአበባን ያምናታል!?

ቅስቀሳው እንዴት እየሄደ እንደሆነ ጠየኳቸው። ሚኒስትሯ ከዋከብት የደመቀ አይኗን ተከለ፤

"የዛሬው የምረጡኝ ቅስቀሳ ቡና አብሮ በመጠጣት ነው ተበሎ ሀያ ሂጂ ሀያ አንድ ስኒ ቡና ተጋትኩ" አሉኞኝ።

ወርቃአበባ ከአፏ ተቀበላት፣

"አየሽ አይደል ገነት! ገኒ! ሴቶቹ እንዴት እንደሚወዱሽ!... ቡ የልደታ ቤተክርስትያንን ችግር እንደምትፈቺላቸው ቃል ስትገቢ የዳዊት ለዘላለም ይግዛን አሉሽ "በማለት ዉሎአቸውን አዳነቀች።

እኔን ደግሞ በጥቅሻ መታችኝ... የልደታዋ ንግስት!... ወርቅአበባ።

ከብርት ሚኒስትሯ ደስ አላት።

ጨዋታችንን ቋጭተን ወደ ስብሰባ አዳራሹ ስንሄድ ወርቅአበባ ኋላ ጉተት አድርጌ፤

"እንቺን ማን ያምናል? በርጫ ወቅጠሽ አጠጣሻት እንዴ? አይኖቿ መያዣ አስፈለጋቸው" አልኳት።

ዙት ብላ አየሳቀች፤

"የእግዜሩን ግምገማ ለማስቀየስ ነው። ታገል (ታገል ጌታቸው ባ ነው) ከቤት ስንወጣ ለእግዜሩ አንብቢለት ብሎ ከሚወደው ገጣሚ ፊ ጽፎ ሰጥቶኛል።"

"እስቲ አንብቢልኝ?"

"የእግዜሩ ስብሰባ ሲያልቅ ገነትን ወደ ኋላ ከስቀሪት አነበልሀለሁ

እንዲህ ነበር የሆነው።

በምርጫ 92 በወረዳ 21/22 ኢህአዴግን ወክላ ለፓርላማ እጩ ሆና የቀረበችው የትምህርት ሚኒስትሯ ወ/ሮ ገነት ዘውዴ ነበረች። አግዜሩ ደግሞ ምርጫውን በበላይነት ከመምራት በተጨማሪ በዚሁ ወረዳ ለከተማ ምክር ቤት እጩ ሆኗል።

ምርጫው ጥቂት ሳምንታት ሲቀሩት የሁሉም ወረዳ እጩዎችን የስራ ሰምሪት ለመስጠት ሜክሲኮ ዞን ጽ/ቤት ጠርተናቸው ነበር። ወይዘሮ ገነት ሀገር ሰላም ብላ በስብሰባው ታድማለች። ጠንከር ያሉ የግምገማ ነጥቦች ሲነሱ እሷም ፀሀዩ መንግስታችንን እንዲጠላ ያደረጉት የበታች ካድሬዎች ናቸው የሚል ወቀሳ አዘል አስተያየት ትሰጣለች። በንግግሯ የተበሳጨው አግዜሩ፤

"... ገነት እኔ ህይወቴን ሙሉ ከህዝብ ጋር እየተገናኘው የድርጅትና ፕሮፖጋንዳ ስራ ሰርቻለው። የህዝብ ሀሳባ አዳምጫለሁ። እውነቱን ንገረኝ ካልሽ እንዳንቺ ህዝብ የሚጠላው ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም፤ ከሁሉም የሚያሳዝነው ስትወድቂ እኛንም ይዘሽ መገንደስሽ ነው፤" አላት።

ከበርት ሚኒስትሯ ተንሰቅስቃ አለቀሰች።ልቅሶው ሲበርድላት፤

"እኔ የኢህአዴግን የትምህርት ፓሊሲ በቁርጠኝነት ከማስፈፀም ውጭ ምን ያደረኩት ነገር አለ? ፓሊሲው ትውልድ ገዳይ እንደሆነ እየገለፀ ያለው ህዝቡና ምሁራኖች ናቸው። እኔ ፓሊሲ የመቀየር ስልጣን የለኝም፤ _ ስለዚህ ህዝቡ የጠላኝ በፓሊሲው ምክንያት ነው። ርግጥ ከኢህአዴግ በተቃራኒ የቆመው ዶክተር በየነ ጴጥሮስ "ዮዲት ጉዲት፤ " የሚል ስያሜ ሰጥቶኝ በህዝቡ ጥላቻ ላይ ቤንዚን ጨምሯል።" የሚል አስገራሚም አነጋጋሪም ምላሽ ሰጠች።

ከበርት ሚኒስትሯ በፓሊሲው ትውልድ ገዳይነት ላይ ጥርጥር የላትም። ባለስልጣናት ልጆቻቸውን ከተቻለ እንደ ሽማግሌው ስብሀትና አርከበ እቁባይ ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ውጭ ሀገር ፣ካልተቻለ ደግሞ የሀገሪቷን የትምህርት ስርአት በማይከተሉ የሀገር ውስጥ ምርጥና ውድ ትምህርት ቤቶች እንደምናስተምር ታውቃለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አስረኛ ክፍል ማለቁ ሀብረተሰባዊ ውግዘት እየደረሰበት እንደሆነ ለሁሉም ግልፅ ነው። ዩንቨርሲቲ ከሚማሩ ተማሪዎች ስማቸውን በአግባቡ መፃፍ የማይችሉ መኖራቸው ሀቅ ነው። የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃትና አለም አቀፍ ተቀባይነት ቁልቁል ወደ ታች እየተምዘገዘገ እንደሆነ የአለት ሪፓርቷ ሆኗል።

እናም ከበርት ሚኒስትሯ ራሷ ባልፈጠረችውና መቀየር በማትችለው ሸውራራ ፓሊሲ ምክንያት "ዮዲት ጉዲት" የሚል ስያሜ ወጥቶላታል።ፕሮፌሰር በየነም ቢሆን የፈሪ ዱላ ካልሆነ በስተቀር ፓሊሲውን ማን እንደቀረፀው

እማዜሩ በበኩሉ የሊቀመንበሩን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በአይነ ቁራኛ መከታተል ይጀምራል፣ ስልኩን ይጠልፉል፣ ማታ ማታ ቢሮውን ከፍቶ በመግባት ደብመንቶችን ኮፒ አድርገው ይወጣል። መላኩ አማተር አብዮተኛ ነበርና ከላይ እስከ ታች የተዘረጋውን የሚስጥር አደረጃጀት አሳልፎ ይሰጣል። ለጥንስሱ መጨናገፍ አስተዋጽኦ ያበረክታል። የፓለቲካ ህይወቱም በዛው ፍጭሚ ያገኛል።

እማዜሩ በዞኑ ውስጥ የሚገኙና ጥበቅ ከትትል የሚደረግባቸውን ተቋማት ማስተር ቁልፍ በማዘጋጀት ደብመንቶችን ያሰርቃል፣ ኮፒ ያስደርጋል። ቢሮአቸው እንዲሰበር ካደረጋቸው ውስጥ በወረዳ 21 ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኘው የአዲሳባ ሴቶች ማህበር፣የልደታ ቤተክርስትያንና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ (ኢሰመጉ) ይገኙበታል። የአዲሳባ ንግድ ምክር ቤት ከእማዜሩ የስለላ ወጥመድ ማምለጥ አልቻለም። የንግድ ምክር ቤቱ የተወያየባቸው አጀንዳዎችና ቃለ ጉባኤዎች በቀጥታ ይደርሱታል። ይህንን የሚፈፅምለት ታደለ ይመር የሚባል በንግድ ምክር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ላይ የሚገኝ ሰው ነበር... ልማታዊ ባለሀብት።

(ታደለ ይመር በንግድ ምክር ቤት ውስጥ የአገልግሎት ዘርፍ ሀላፊ ነበር። ይ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሆነ ሰው በካድሬው ዘንድ "የእርጉ ዝንባ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር። የምይገኝበት ቦታ የለም። በኢትዮጵያ ታሪ ውስጥ አሳፋሪ ተግባሮች ከፈፀሙ ሰዎች አንዱ ነው። በተለይም በኤርት መገንጠል ወቅት የኢትዮጵያን ህዝብ ወክለ ተበሎ ኤርትራ በመሄድ " አ የኢትዮጵያ በተለይም የአማራ ተወላጅ የሆንን ሰዎች ስለፈፀምንባችሁ ግፋ በደል ይቅርታ እንጠይቃለን" የሚል ንግግር አድርጓል። ቅሌት እንዴ ከተጀመ አያልቅምና የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሲጀመር ደግሞ ንግድ ምክር ቤ በመወከል በየአዳራሹ "ሻአቢያ ይደመሰሳል፣ የኤርትራ ህዝብም ልኩን ያውቃ የሚል ቀራርቶ አሰምቷል...

ታደለስ ታድሏል...
የማይጣላ ጭንቅላት
ተሸክሞ ይዞራል።)

እማዜሩ ትላልቅ የሚባሉ የኢህአዴግ ካድሬዎችን ሳይቀር ደም አ አስለቅሷል። የአምባሳደር ገነት ዘውዴ የልቅሶ ታሪክ ጅማሬ በአማ አማካኝነት ነበር።

ኢህአዴግን የሚያሸብር እንደ ሽብርተኛ ይቆጠራል የሚል እንቀጽ እንደሌለው ገልጫለሁ።)

***

ወደ ወረዳ 20 (ቁራና ገፅ) ያመራው ካድሬ የተቃዋሚ እንድ አጨ አሸዋጥቶም፣ የግል ተወዳዳሪዎች በግፉ አስገብቶም ሳይሳካለት ቀረ። የወረዳ 20 ህዝበ ኢህአዴግን ከፓርላማም ከአዲሳባ ከልል ምክር ቤትም አባረረ። ያቁራና ገፅ ህዝብ ኢህአዴግ ያቀረበለትን ዶክተር፣ ኢንጂነር፣ ጋዜጠኛና ከፍተኛ ነጋዴ ወደ ገን ትኑ መቃበራቸው የተማሰ፣ በምርኩዝ የሚሄዱ፣ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ የመኢአድ አባላትን መረጠ። ይህም ህዝቡ እንደ ወረዳ 24 ሁሉ ኢህአዴግ ላይ ያለውን የመረረ ጥላቻ ጭንትው አድርጐ የሚያሳይ ሆነ። እንደ እውነቱ ከሆነ የሰምአን ልጅም ሆነ አቶ መለስ ወረዳ 20 መኖተው ቢወዳደሩ ኖሮ ወይ ለከበራቸው ሲባል ኮሮጆ አሰቀድሞ ይገለበጣል፣ አሊያም የሽንፈት ጽዋቸውን ይጐነጫሉ።

***

የወረዳ 21/22 ነዋሪም ተመሳሳይ እርምጃ የወሰደ ቢሆንም በቆጠራው ወቅት በተሰራ ማጭበርበር ኢህአዴግ ተረፈ። በወረዳው የትግራይ ተወላጅ ይበዛል በማለት "የትግራይ ህዝብ በወረዳ 21 ኢህአዴግን ታደገ" የሚል ማጭበርበሪያ እንዲናፈስ ተደረገ።

የወረዳ 21/22 ምርጫ እንዲመራ የተመደበው ነባር የህውሃት ታጋይ ገ/እግዚአብሔር "እማዜሩ" ይባላል። መጠሪያውና ግቡሩ ለየቅል የሆነ ሰው!!

አንዳንዴ ስም ሰይጣን ያወጣዋል።

የካዛንችሱ ስውር መንግስት ለእማዜሩ ተነግረው የማያልቁ ወንጀሎችን እንዲሰራ ሙሉ ስልጣን ሰጥቶት ነበር። እማዜሩ በስርአቱ ውስጥ ካሉት ሶስት ቁልፍ የዞን ካድሬዎች አንዱ ነበር። መቀመጫውን ሜከሲኮ በማድረግ ሰቅጣጭ ግፎችን ሰርቷል። ብዙ ሰዎችን ያለወንጀላቸው አሳስሯል፣ ከስራ አባሯል፣አገር ጥለው እንዲወጡ አድርጓል። የግለሰቦችን፣ መንግስታዊና መንግሲታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቢሮዎችን በለሊት በመከፈት አስበርብሯል፣ ዶክመንት ኮፒ አድርጐ አስወጥቷል።

በእማዜሩ የስለላ መዋቅር የመጀመሪያውን ገፈት የቀመሰው የዞኑ ሊቀመንበር የነበረ መላኩ የሚባል ካድሬ ነበር። መላኩ በከተማዋ በህቡዕ የተቋጣጠለውን የጉራጌ መራሽ አብዮት ከሚመሩት የጉራጌ ልጆች አንዱ ነበር። የአብዮቱ ጥንስስ ወደ አመፅ ተቀይሮ በትላልቅ ሰልፎች መታጀብ ሲጀምር (መስቀል አደባባይን ጨምሮ) መላኩ ግንባር ቀደም መሪ ነበር።

"የሚገርም ነው። አየሞሸኽኝ እንዳይሆን?"

"ለምን እሞሸህለሁ! አናንተ ኪሮስንም ሆነ ዳኛ ልዑ አታውቋቸውም። አስቲ ልጠይቅህ? ምንም አይነት ስራ የሌለው ሰው እንደ በየቀኑ ውስኪ ያወርዳል። ኪሮስ ከየት አምጥቶ ነው?

"...በጅማ ሰፊር ዳኛ ልኡል "ትንሹ መለስ ዜናዊ" እንደሚ ታውቃለህ? ከዳኝነቱ በላይ ቀበሌ አካባቢ ብዙ ገንዘብ ያገኛል። እ ልጠይቅህ? አንድ ትልቅ ዳኛ ቀበሌ ወርዶ የሚርመጠመጠው ለ ይመስልሀል? ቀበሌ ከመደባት ካድሬ መሰረት ጋር ሲንጐዳጐድ እጅ ከፍ መያዙን ካልዋሸኽኝ በስተቀር በሚገባ ታውቃለህ።"

በድጋሚ አቋረጥኩት፤

"የህጣ ሰርአቱ አለኝ የሚለውን ትልቅ ሰው ሰም እያጠፉህ እንደ እወቅ።" አስጠነቀቅኩት።

በፈገግታ ውስጥ ሆኖ፤

"የቀበሌውን ሊቀመንበር ዘይኑን ቀሰ ብለህ አውጣጣው። እ ያወቀውን ፀሀይ የሞቀውን ሀቅ ይነግርሀል።የመረጃ እጥረትህን ይሞላልህ ውሸማና ሚስትን ያስታረቀው አሱ ነው። ልኡል አንኳን ለናንተ ሰባት ሚ የማግባት አቅም አለው በማለት።"

አበበ ቀስቶ ሲስቅብኝ አመሸ።

(ዳኛ ልኡል ገ/ ማርያም በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተ ችሎቶች በሰብሳቢነት ሰርቷል።ማለሰቡ ህገ መንግስቱን በጣስ ሁኔታ በወረዳ ቀበሌ ነ ውስጥ የህውሀት አባል የነበረ ሲሆን በቀበሌው የሚመደበ ካድሬዎች የሚመለምለው አሱ ነበር። ዳኛ ልኡል ከፍተኛ የአቅም ችግር ያለ ቢሆንም በሀገሪቱ ወሳኝ ተቡለው የሚታወሱ ከሰቶን ዳኝነት መርቷል። ያ አፍሮ በመኪና ሰው ገጭቶ የማምለጥና በምርጫ 97 የታሰሩ የቅ አመራሮችን ከስ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። በምርጫ 97 የቅንጅት ከሰ አቃቤ ህግ የነበረው ሽመልስ ከማልና የቴዲ አፍሮ ጠበቃ ሚሊዮን አስፋ ከሚንቋቸው ዳኞች ዋነኛው ልኡል ገ/ማርያም ነው። ሽመልስ ዳኛ ልኡ ከአቶ መለስ በላይ ህውሀትነቱን ለማሳየት የሚተጋ ባዶ እንቅብ!" ይለ ሚሊዮን በበኩሉ፡" ባጣ ቆየኝ!" ብሎ ይጠራዋል።

እነሆ! ልደቱ በቀበሌ ደረጃ ለወረዳ ምክርቤት ተወዳድሮ ተሸ ለሽንፈቱ ትልቅ ሚና የተጫወተው አበበ ቀስቶ ለቀበሌው ህዝብ ያደረ ንግግር ነበር። ይህም የወረዳውና ቀበሌው ህዝብ ከልደቱ በላይ አበበ ቀ እንደሚሰማ አመላካች ነበር። እንደ አውነቱ ከሆነ አበበ ቀስቶ የህዝብ የሚያመው ትንታግ ታጋይ ነበር። ከጅማ ሰፊር እስከ ሚክሲኮና ስድስት በእግሩ እየሄደ የሚያስተጋባ። አበበ ቀስቶ የህዝብ አይንና ጆሮ ነበረ... የነዋሪ ምሬትና እንግልት በአደባባይ የሚያጋልጥ። አበበ ቀስቶ የኢህአዴግ ካድሬ ንቅዘት እየተከታተለ የሚያጋልጥ አሸባሪ ነበር። ኢህአዴግን በማሸበሩ ምክ በሽብርተኝነት ተከሶ ወደማይቀርለት ወህኒ ወረደ። የፀረ ሽብርተኝነት አ

ደረጃ። በዛ ላይ የሚጣራበት ነገር አለ፣ እውነት ከሆነ ከድርጅታችን
ዋለን ማለት አልነበረብህም። በጭጥ ደረጃ ተወዳድሮ ቢሸነፍ ትልቅ
ነው።"
እንዲህ በማለት ተቃወመኝ፣
"አየህ ኢዴአፓ ከኢህአዴግ የሚለየው በዚህ ነው። ከድርጅት ጥቅም
ህዝብ ፍላጎት ያስቀድማል። አዲሳአባ ከመቶሺህ በላይ የቀበሌ ቤቶች
ነኑ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለባለቤቱ እንመልሳለን ብንል እንዴት
። ይሄ ሁሉ ህዝብ የት ይሂድ። በምርጫስ እንዴት እናሸንፉለን?...
ሚያደርጉት በዘረኝነት የታመመው የእናንተ ሊቀመንበር መለስ ዜናዊና
ነው ናቸው። ወያኔ ትግራይ ላይ ተግባራዊ አድርጓል።"
ቢራውን እየተጎነጨ፣
"... ልደቱ ኢዴአፓን ለማፍረስ ከደህንነት ቢሮ የተላከብን እንደሆነ
ለን። ከታቦት ስርቆት ጋር በተያያዘ መረጃዎች ደርሰውናል።የደህንነቱ
ህን ካርድ መዘ በማሳየት ልኮታል ብለን እናምናለን።አስተማማኝ ማስረጃ
ለህዝብ ይፉ እናደርጋለን በዛ ላይ ልደቱ የስልጣን በር ካየ በከላሸ
ን እንደሚሄድ እናውቃለን። ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ
ታችን ሚስጥር እየወጣ ነው።መረጃውን የሚያሾልከው አሱ ነው የሚል
ኔ አለን። የልደቱ የኋላ ታሪክ የቆሸሸ ነው።"

በድጋሚ ለረጅም ደቂቃ ፀጥታ ሰፈነ። ቢራዎች ተንደቀደቁ። እኔ ሞቅ
አበበ ቀስቶ ሰከረ።
ወጋችንን ለመቀጠል፣
"በምርጫ ፵፭ የዶክተር ጶፊቅን ብር ቀርጥፈህ መወዳደርህ አስከ
ው ይደንቀኛል። አለመፍራትህም ገርሞኛል" አልኩት።
ነመች በሄደች አይኑ አያየኝ፣
"ለምን እፈራለሁ? በምርጫ ሀጉ ከለላ አግኝቻለሁ። እንደምታውቀው
ስትሆን ከባድ ወንጀል ስትፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዝክ በስተቀር
ም። እንደማሸንፍ እርግጠኛ ስለሆንኩ የህግ ከለላው ለሚቀጥሉት
ኑ አመታት ይቀጥላል።ገንዘቡን በተመለከተ የሚገርምህ ለራሴ እምስት
ው አልተጠቀምኩም። አሰር ሺህ ብሩን በሙሉ ምርጫ ለቀሰቀሱልኝ
ች አከፋፈልኩት።"
"አሰር ሺህ? የተቀረውስ?"
"ምን ቀረና። ኪሮስ አይናማውና ዳኛ ልዑል ገ/ማርያም መጀመሪያ
ኒህ ፡ቀጥሎ አምስት ሺህ ብር ሰጡኝ። እምቢታዬን ስገልጽላቸው
ትሺውን ማንቁርቱ ላይ ቆመው ወሰዱ።"
"እንዴ?"
በመገረም እያየኝ፣
"ለሁለቱ የወያኔ ሌቦች ብዙ ብር እንደሰጣችሁ አውቄያለሁ።
ራእንደኛው ሰእት ሀያ ሺህ ብር ልጨምርለህ ብለውኝ ነበር። አይሆንም
።።"

አይፈቅድም።"

አበበ ቀስቶ ተወዳደረ። አሸንፎ ተሸነፈ።

ከአለታት በአንዱ ቀን ምሽት ቀበሌ ፲፩ መዝናኛ ከበብ ስገባ አበበ ቀስ
ቁጭ ብሏል። ከእጁ የማይለያትን የኢትዮጵያ ባንዲራና የምርጫ ምልክ
የሆኑትውን ጭራ ተሸክሞል። ከቀናቶች በኃላ ለሚካሄደው የወረዳ ምክር ቤ
ምርጫ እጩ ሆኖ ቀርቧል።

በመዝናኛ ከበቡ አንድ ሁለት ቀዝቃዛ ቢራ ጠጥቼ ሂሳብ ለመክፈ
ስጠይቅ አበበ ቀስቶ አስቀድሞ ከፍሎልኛል። ሂሳቤን ሳላወራርድ መሄ
ስላልፈለኩ የቢራ ጠርሙሴን ይዤ ወደ እሱ ሄድኩኝ። እንዲህ በማለት ጨዋ
ጀመርኩ፣

"ምርጫ 92 በዝረራ ስትሸነፍ ከአንግዲህ ፓለቲካ በቃኝ የምት
መስሎኝ ነበር።" አልኩት።

አበበ ሳቀ። ተንተከተከ። ሳቁበኝ።

በማሾፍ አያየኝ እንዲህ አለ፣

"እናንተ እኮ ጅሮ ሰለሌላችሁ ነው። አይደለም የወረዳ 24 የአዲሳ
ህዝብ አንቅሮ ተፍቷችኋል። የተተፋ ምራቅ ደግሞ ተመልሶ አይዋጥም።"

"ምን ማረጋገጫ አለህ?"

"ቅዱስ መጽሀፉ እሹ ይለጣችኋል አይደል የሚለው። የሲጋራ ሱ
ሲጋራ ቸግሮት አይተህ ታውቃለህ? እኔም የመረጃ ጥማቴ እንደዛው ነው።"
ለጥቂት ደቂቃ በዝምታ ከቆየን በኃላ እንዲህ አልኩት፣
"ልደቱ አያሌውን ቀራንዮ በምትገኝ ቀበሌ 17 ወርዶ እንዲወዳደር ያደረከ
አንተ ነህ ይባላል?"

"እናንተ መያኔዎችና ልደቱ አንድ ናችሁ። የስልጣን ጥማታችሁ እው
አድርጓችኋል። ልደቱ በባዶ እውቀቱ እየተኮፈሰ እንደሆነ ለማሳየት ነው ቀ
የወረወርነው።" አለኝ።

"ቢሆንም ፍቃደኛ ሆኖ እየተወዳደረ ባለበት ሁኔታ ልትደግፈው ይ
ነበር። ህዝብ በተሰበሰበበት አዳራሽ ለምን አዋረድከው። መልስ እንዳይ
ይግም ሌላ ቀበሌ ላከው።"

ቢራውን እየተጎነጨ፣

"እየህ ልደቱ ጅሮ ለማግኘት ብለው በድርጅታችን ፕሮግራም ወ
የሌለ ነገር እንደ ፓርቲያችን አቋም አድርጎ እያቀረበ ነው። ኢዴአፓ የቦ
ቤት ለባለቤቱ እንመልሳለን የሚል አቋም የለውም። እሱ ግን በእደባዩ እን
ብለው ተናገረ። ለወያኔ ትልቅ በትር አያቀረብክ ነው ብዬ ብቆጣው አልሰ
አለ።ያለኝ አማራጭ እሱ የሚወዳደርበት ቀበሌ 17 ሄጀ ውሸቱን እን
መግለጽ ነበር። ይህን አድርጌያለሁ።"

አቋረጥኩት፣

"ቢሆንም ልደቱ ፓርቲያችሁን ወክሎ እየተወዳደረ ነው። ያ

ሚሊዮን ብር ነው።" በማለት መልስ ሰጠ፣ "የካቢኔ አባላት አብራችሁ ነዋ የዘራችሁት?" በድጋሚ ጠየቀው።

"አማርኛህን አስተካከል! በካቢኔ የመወሰን ስልጣን አለን።" ሽሮው ደነፋ።

"ካቢኔውን ወደ አይን ያወጣ ዝርፊያ የወሰደከው አንተ ነህ። ይባስ ብለችሁ መሀል ቦሌ ላይ የህዝብ ንብረት ትዘርፉላችሁ?"

አሊ ተናደደ፣

"ስነስርአት አድርግ ዘርአይ! ...ዘራፊ እንድትለኝ አይደለም እዚህ የተቀመጥኩት። ሀቁን ተናገር ካልክ አንተን እንዲህ ያበሳጨህ ሌላ ነገር ነው። እንጉን ጨምሮ የፊዴራል ተቋማት ኢህአዴግ ኮሚቴዎች እኔ ጋር መጣችሁ ለእኛም የቢት መስሪያ ቦታ ስጠን ብላችሁ ጠየቃችሁኝ። ደብዳቤ ፅፋችሁ እያጠፋ በካቢኔ አናየዋለን አልኳችሁ። በተለይ አንተ ወደ ኃላ ቀረት ብለህ ደብዳቤ መግፍ አደጋ አለው ድርጅቱ ሊሰማ ይችላል አልከኝ።"

አዳራሹ በሳቅ ተሞላ...

ለባለጌ ገድሉ ውርደቱ!

አባይ ግምግማው አቅጣጫ እንዳይስት በማሰብ፣

"የዘርአይን በራሱ ጊዜ አናየዋለን። እነ አሊ ቦሌ ላይ መሬት የተቆራመታችሁት ወንጀል ነው። እርምት ካልተወሰደበት በህግ ሊያስጠይቅ ይችላል። ለጊዜው ስለ ህግ የምናወራበት ሰአት አይደለም። እኔ ባለኝ መረጃ የተዘረፈው መሬት የትምህርት ቤት ቦታ ተቆርጦ ነው፣ ይህ ደግሞ የከፋ ያደርገዋል።" አለ።

አጠገቤ የተቀመጠው ፍስሀ "አባይ መቋጠር ጀመረ" ብሎ ማስታወሻዬ ላይ ፃፈ።

ቀጥሎ ለደህንነት ሀላፊው ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ ተሰጠው። ኢሳያስ የደንቁርና አክሊል ያጠለቀ የአቶ መለስ የቁርጥ ቀን ልጅ ነው። እንደለመደው በአብሪት የታጨቀ ስድብ ካቀረበ በኃላ በማጠቃለያው፣

"አሊ አዲሳባን የመሰለች ውስብስብ ከተማ ቀርቶ ወረዳ ለመምራት ብቃት ያንሰዋል። በዛ ላይ ዝርክርክ ነው" አለ።

አባይ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ትችት አቅርቦ ማሳረጊያውን "አሊ ዝርክርክ ብቻ ሳይሆን ደንታ ቢስና ዘባተሎ ነው" በማለት አጠናከረ...

ዝርክርክ ! ... ዘባተሎ!!

አሊ በተቀመጠበት ወንበር ሲፈረካከስ ተመለከትኩት።

የአለቱ ግምግማ በዚህ የአባይ ቃል ተፈፀመ።

ምእራፍ ሰባት

ዘባተሎው መሪ!

"ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ፣ አለ አሊ አብዶ አላየሽም ፣
(ሪፓርተር ጋዜጣ)

ዝርክርክ! ዘባተሎ! ደንታ ቢስ!

በጨፌ እየተካሔደ ባለው ግምገማ አጠቃላይ ችግሮች ኑ
በጋላ ወደ ግለሰብ አውጫጭኝ ተገባ። የመጅመሪያው አቅራቢ አሊ
ሆነ። ሰውየው ተደናግጧል። በከተማው ማንባር ቢታ የገነባው ቪላ
አንቅልፍ ነስቶታል...

አይውጠው ነገር...!

ቢሆንም ግን አልሞት ባይ ለመሆን አይኑን በጪው አጥቦ
ዘላበደ... የሙስና ችግር እንደሌለበት፣ ለጥቅም የዘረጋው ኔትወ
ንደሌለው፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ለመቀበል ችግር እንደሌለበት አረ
ቁልፍ ችግሩ "አደራጅቶ መምራት ያለመቻል" እንደሆነ ገለፀ።

ርግጥም ተምታቶበታል...

ሽሮ ቢደነቍ እንጀራ እስኪቀርብ ነው!

አባይ አሊ ያላነሳው ነገር ካለ ቤቱ እንዲያሳየው አድል ሰጠ፣
አቀራረብ መናደዱ ያስታውቃል። ሁለት እጅቹ ቀድመው
ማካሼሊያኖቹ ዘርአይ አስማዶምና ኢሳያስ። ለዘርአይ አስቀድሞ ተሰጠ
ዘርአይ ስራውን እንዲህ በማለት ጀመረ፣

"አሊ! የዝች ከተማ መበስበስና መብከት ተጠያቂው እን
ከሙስና የፀዳው ነኝ የምትለው ቦሌ የነባሽው የሁለት ሚሊዮን
መሬቱንና ግንዘቡን ከየት አምጥተህ ነው?" በሎ ጠየቀው።

አሊ በበኩሉ፣

"... መሬቱን ህጉን በተከተለ መንገድ በካቢኔ ውይይት ተ
በአብላጫ ድምፅ ተወስኖ ነው። ብዙዎቻችን ወስደናል። ቤቱን የሰራሁ
ሀገር ባሉ ዘመዶቼ እርዳታ ነው። የተሰራው ዘርአይ እንደምትለ

እንዲህ ነበር የተደረገው።

በአበዛኛው ምርጫ ጣቢያዎች የተቃዋሚ ታዛቢዎች ባለመኖራቸው ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ ለሊት ዘጠኝ ሰአት ተቋረጠ። ምክንያቱ ደግሞ ምን ሰለተዳከሙ አረፍት አድርገው ይምጡ የሚል ነበር። በከተማዋ ግራን ካድሬዎች በየዞናችን በማደር የአዲሳባን ውጤት በየደቂቃዉ ሰለነበር አስደንጋጭ ውጤቶችን መስማት ጀመርን። የመጀመሪያው የዞረራ ዋልዋ መሸነፍ ሆነ። ለዋልዋ ልጅ ከልቤ አዘንኩኝ። ከፊቢያዊ ማእከላዊነት አስረኛ እንደሆነ ስለማውቅ።

ቱፐሎ የደረሰን የአሊ አብዶና ካቢኔዎቹ ሆነ። ሁሉም ላይ ህዝቡ እሳርፉል፡ ካለድ (ም/ል ፕሬዝዳንት)፣ ታጋይ ማሚት (አስተዳደር ጣይቱ (የምክር ቤት ሀላፊ)፣ ቶፊቅ (ኢኮኖሚ ዘርፍ) ዘመዳ (የካቢኔ በዝረራ ተሸንፈዋል።

ጠዋት ታዛቢዎች ተመልሰው ቆጠራ ሲካሄድ የነበረው እንዳልነበር ኮሮጆዎች ግልብጥብጣቸው ወጣ። አሊና ካለድ ቶፊቅ፣ ጣይቱንና ን ትተው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ከመሀል ኮከብ ያላትን ባንዲራ ሰበሰቡ ማዘጋጃ ቤት ገቡ።

መለስ ያደራጀው አሱ እንደሆነ ሞንጀሪኖ አጋለጠች። የህቡዕ አደረጃጀቱ ማ
ማታ ስብሰባ ሲያደርግ የነበረው በሜክሲኮ እንደሆነ ተረጋገጠ። ማምለ
መንገድ ሲያጣ አቶ መለስን ይቅርታ ጠየቀ። አቶ መለስ እንደ ሌሎ
አልራራለትም፣ "በዛን ቢላዋ የድርጅቱን አንገት ዘከዝከህል" ብሎ በቅጣ
መልኩ የትግራይ በረሀ ሰደደው።

እግዜሩ ለሶስት አመት ያህል የትግራይ ተራራን ሲቧጥጥ ከረመ
መስመር ማስተካከሉና እርምት መውሰዱ ሲረጋገጥ የተዘጋጀለት የመ
ፋይል በጐንዮሽ እንዲደርሰው ተደረገ፣ "ሲያዩህ ሌባ ትመስላለህ" ብ
እንዳላባረረ የእሱ ንቅዘት የማያልቅ ሆኖ በፋይል ተጠርዞ ተሰጠው። በየአ
በሚሊዮን ብሮች የሚዘረፍበትን የአየር ጤና ኪላ (ጉምሩክ) ሀሩይ የሚ
የቅርብ ዘመዱን ሀላፊ አድርገው ሲያሰራ እንደነበር፣ ሲኖርበት የነበረውን የቀ
ቤት ለወንድሙ ሰም አዙሮ መስጠቱ፣ ኤርትራዉያን ናችሁ በማለት ቡ
ከሺላ ቤታቸው ካፈናቀለ በኃላ እሱ ገብቶበት መኖር እንደጀመረ፣ በምርጫ
ማግስት ኮልፌ ቀራንዮ ላይ አርከበ እቁባይ አይን መሬት እንደሰጠው።

እናም እግዜሩ ይህንን የታሸገ የመሰና ፋይል ይዞ አዲሳባ መጣ።
መለስ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቭዥን የትግርኛ ፕሮግራም ዋና ሀላፊ እድ
ሾመው።የአድርባይ ፊትአውራሪ ከሆነው ዘርአይ አስክዶም ጋር ተቀላ
የኢቲቪ የትግርኛ ፕሮግራም ከአንጨትነት ወደ "አሞራ ሲጋት" ተቀየረ...
እምበር ተጋዳላይ!!

***

እኔና ፍስሀ በራስ ሆቴል ውይይታችን በቀጥታ ከመራናቸው እ
ወረዳዎች ተሻግረን ወደ ሌሎቹ ሄድን። በአብዛኞቹ በከፉ ሁኔታ ፀረ ጂሞ
ድርጊቶች የተፈፀመባቸው ነበሩ።በተቃዋሚ አፈጩነት ይመዘገባሉ ተ
የተጠረጠሩ ነዋሪዎች አስከመታሰር የተካሄደባቸው፣ አፈጩ ሆነው ከተመ
በኃላ የስም ማጥፉት ዘመቻ ተካሂዶባቸው ረሳቸውን ያገለሉ፣ ተቃዋ
የምርጫ ታዛቢ እንዳይኖራቸው የተደረገበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። በ
በአዲሳባ በሚገኙት 29 የገጠር ቀበሌዎች የተካሄደው ምርጫ አሳፋሪ
የኢህአዴግ ታዛቢ ብቻ የነበረበት ምርጫ፣ ምርጫ አስፈጻሚው፣ ፉሪ
ታዛቢው በሙሉ ኢህአዴግ... የገጠሪቷ ኢትዮጵያ ትንሹ ግልባጭ።

ይህ ሁሉ የማጭበርበር ስራ ተሰርቶ በነጋዴውና ህዝቡ የተሳ
አነ አሊ አብዶና ምክትሉ የነበረው ካሊድ አብድርህማን የሸንፈ
ተገንጭተዋል። ምንም እንኳን በቆጠራው ሰአት በሰሩት አከርካ
ምክርቤት ቢገቡም።

ው ወረቀቱን መነጨኳት።

በጠራ ጨረቃ በኩለ ለሊት፣
አይናቸዉ ሲያበሩ እንደከዋከብት፣...

ርስው መለስኩላት። በቃሌ አነበንበኩት።
አንቲን አየነቀነቀች "አንተና ታገል?..." አለች።
"ይልቁንስ ቅድም የዳዊት ዘር? ምናምን ያልሽው። አልገባኝም?"
"ተዋት ባክህ! የልደታ ህዝብ ምን እያለ እንደሆነ አላወቀችም!" በማለት
እየቆጠረች ዘረዘረች፣
አፈ ጉባኤ ዳዊት ዮሀንስ የሚኒስትር ገነት ዘመድ፣
የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዶ/ር ከበደ የሚኒስትር ገነት ባለቤት፣
የምርጫ ቦርድ ሀላፊው አሰፋ ብሩ የሚኒስትር ገነት ዘመድ፣
የኢሲላባ ካቢኔ ወይዘሪት ጣይቱ አሊ የሚኒስትር ገነት እህት...

ከብዙ አመታት በኋላ እኔም በተራዬ ለወርቃአበባ በቀጭኑ ሽቦ እንድ
ኳላ በቀኝ ጨምሬ ነገርኳት፡-
የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ጭንቅላት ገነነ አሰፋ የአምባሳደር ገነት
፡ የኢህአዴግና የበረከት ራስ ምታት ፕሮፌሰር ዳኛቸው አሰፋ
ደር ገነት ወንድም ...
የዳዊት ዘሮች...
ዘላለም ይግዙን!

***

እግዜሩ በቂርቆስ የትግራይ ተወላጅ ስለሚበዛ ኢህአዴግ በአብላጫ
እንደሚያሸንፍ አስቀድሞ እንዲነገር አደረገ። የምርጫ አስፈፃሚዎችንና
ጃችን ከድርጅት መለመለ። ምርጫ ቦርድን ተክቶ አረንቴሽን ሰጠ።
ነ ሀይሉን በስም ዝርዝር ለይቶ በየጣቢያው አስመደበ። የወረዳ 21/22
የምርጫ ክሮጅ አስቀድሞ ተገለበጠ። ተቃዋሚዎች መረጃ ደርሷቸው
ጫ ቦርድ ቢያመለክቱም በሬ ወለደ እንደሆነ በምርጫ ቦርድ ሀላፊው
ብሩ መማለጫ ተሰጠ...
የዳዊት ዘር!

***

የእግዜሩ የመጀመሪያ መጨረሻ ...

እግዜሩ የኳዘንቸሉ መንግስት ሲንኮታኮት አብሮ ወደቀ። በአዲሳባ የእነ
ደን ቡድን በመደገፍ ቀንደኛ ሆኖ ወረቀት የበተነውና ካድሬውን በፀረ -

ፓሊሲው አንዳችም እንከን የማይወጣለትና ድርጅቱ ተጨንቆ ተጠ
ያወጣው እነደሆነ በመቆጣት ገለፀ። የኤርትራ መንግስትም ሆነ ህዝብ የጥ
ፍላጐታቸውን ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ምንም ግንኙነ
እንደማይኖር አሳሰበ። ግብፅንም በተመለከተ በአይነ ቁራኛ እየተከታተልናቸ
መሆኑንና እኛም በበረሀ የሚዋጋ ሰራዊት እንደምናዘጋጅ ሊያወቁ ይገባል አሰ
ተቆጥቶ!

አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው የካዘንችሱ መንግስት አባል የሆነው ፍ
መአሲ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ፣

"ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ያለው ትክክል ነው፣ የጠላት አስተያየት ብ
ማጣጣል አልነበረብንም። ይሉኝ ሰውዬ የሚረባ አይደለም። የአስተሳ
ዴኩማንነቱን አሳየ። ሌላው ቢቀር ሻዕቢያንና የኤርትራ ህዝብን መለ
አልቻለም አለኝ።

(በዛን ሰሞን የአዲሳባን ማስተር ፕላን ከመፅደቁ በፊ
ለመተቸት ኤግዚብሽን ማዕከል የምሁራን ስብሰባ ተጠርቶ ነበር።
ስብሰባ ላይ የተገኘው ዶክተር ብርሀኑ ማስተር ፕላኑ ሊያ
የሚችል እንደሆነ፣ ግን ደግሞ በአሊ አብዶ ብቃትና ችሎ
ይፈፀማል የሚል እምነት እንደሌለው በግልፅ ተናገረ። የያ
አስተያየት በአህዴድ ደጋፍ ቁጣን ቀሰቀሰ። ዶክተሩን በረከት ስም
ልኮት እንደሆነ መነገር ተጀመረ። በወቅቱ መልካም ግንኙ
እንደነበራቸው ይወራ ስለነበር... የዛሬን አያድርገውና!... ግራም ነ
ቀኝ የዶክተሩ ቃል በተግባር ተፈጽሟል።)

በዉጭ ጉዳይ ፓሊሲው ላይ አስተያየት መስጠት የጀመረው ያ
ተቀዳ አኔን ደግፎ ተናገረ። አንድን መንግስት መቼም ቢሆን ዘላቂ
አድርጐ ማስቀመጥ የተለመደ ፓሊሲ እንዳልሆነ። በሚስጥር መያዝ ያለ
አውነቶች በተለይም ወታደራዊ መረጃዎች በመንግስት ከሚገለፁ
በሌሎች አካላት ቢነገሩ ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ መልዕክቱን ማስተ
እንደሚቻል አስረዳ። ከልምድ አኳያም ቢሆን ሀገሮች የመንግስት ተ
ፓርቲዎችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑና ለሀገር ተቆርቋሪ የሆኑ ድርጅቶ
የሚዲያ ተቋማትን እንደሚጠቀሙ አብራራ። የውጭ ጉዳይ ፓሊ
ባጠቃላይ ከአረብ ሀገሮች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በስጋትና ጥርጣሬ
አንዲቃኝ ማድረጉ አግባብ እንዳልሆነ ገለፀ።

በሳይ የህዝብ ፖንዙብ ቀልጧል። ህገመንግስት የሚንዱ መመሪያዎች ወጡ በማድረግ ነዋሪው ከአካባቢው እንዲፈናቀል አድርጓል። የከተማው በማያቋርጥ የድህነትና በሽታ አደት ውስጥ ገብቶ እንዲማቅቅ የእሱ ከፍተኛ ነው። በከተማዋ የተካሄዱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በሱ አሊያም አድርባይነት የተፈፀሙ ናቸው።

ስለዚህም ይህንን የሰውየውን ጥፋቶች ገለጥለጥ አድርጐ ማሳየት ሂ መስሎ ስለተሰማኝ አስተያየት ለመስጠት የመጀመሪያው የመዲናይቱ ሆነኩኝ። አሊ በእኔ ላይ የፈፀመውን በደል ስለሚያውቀው የእኔ አጅ ግያ ተቀስሮ ሲያይ ደነገጠ። እንደማለቀው ገብቶታል። በርግጥም አንድ ሰፈረኝ ቁና እንድሰፍረው አምላኬን ተማፅኜ ነበር። የጨፈ ግምግማ ን ድበቅ አላማ ባልደግፈውም የሰውየውን ነውረኝነት ለመግለፅ ከዚህ እድል አላገኝም። የመናገር አድሉ ተሰጠኝ። ተረጋግቼ ነጥብ በነጥብ ዘኩ ። አንገቱን ደፋ። ለጨፈው በአጭሩ የተናገርኩት፣ በግል ማሰታወሻዬ ዘለግ አድርጌ የፃፍኩት ወግ የሚከተለውን ይመስላል...

***

ሮኬት ሳይንስ***

እኔና አሊ አብዶ መጀመሪያ የተጋጨነው በውጭ ጉዳይ ፓሊሲ ስልጠና በር። ስልጠናውን የሚሰጡን እሱና የወጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሩ ኮቀዳ አለመ ነበሩ። ከዶክተሩ ገለፃ ቀጥሎ በነበረው ውይይት በፓሊሲው የሱኝን ሁለት ልዩነቶች አንስቼ ተከራከርኩ። እነዚህም ፓሊሲው ኮራ መንግስትና በግብፅ ላይ ያስቀመጠውን የተመለከቱ ነበሩ ...

የወጭ ጉዳይ ፓሊሲው ከኤርትራ መንግስት ጋር መቼም ቢሆን ሰላማዊ ነት አይኖረንም ይላል። ግብፅን በተመለከተ ደግሞ በሚስጥር አሊያም ግስት ደረጃ መገለፅ በሌለበት መልኩ ተፅፉል። ግብፅ የኢትዮጵያ ቴጂክ ጠላት እንደሆነችና፣ ሀገሪቷ ጫካ ሳይኖራት 50 ሺህ የሽምቅና ተዋጊዎችን አሰልጥና ዝግጁ ያደረገችው ለማን እንደሆነ ሳይታለም ታ እንደሆነ ያሳስባል። በመሆኑም ከግብፅ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ይህን ት ውስጥ ያስገባ ሊሆን እንደሚገባ ይገልፃል።

እኔ በበኩሌ ፓሊሲ በአጭር ጊዜ አይታና ስሜታዊነት መሳፍ የለበትም ። ኮራ መንግስትም ሆነ ሻዕቢያ ሊቀየሩ የሚችሉበት እድል ዝማ መደረግ ኮም የሚል ነበር። ግብፅንም ቢሆን ከመልካም ግንኙነትና የጋራ ጥቅምን የት ይልቅ ለነዱ ፀበ አጫሪነትን ያሳያል የሚል ነበር።

ለቃል አቀባይነት የተመረጥነው እኔና ሉልሰገድ ወደኋላ እንድንቀር
ተነግሮ ሌላው ተበተነ። እንድንቀር የተደረገው ከኢህአዴግ ቢሮ ጋዜጠኞች
አየመጡ ስለሆነ የእለት ውሎውን እንድንገልፅላቸው እንደሆነ ተነገረን።
አፍታም ሳይቆይ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አዘጋጅቹ ሴኩቱሬና ፍሬህይወት
አያሌው ተያይዘው መጡ። ውሎውን በጥቅሉ ነግረናቸው በግለሰብ ደረጃ
እየተነሱ የነበሩት ማጠቃለያ ስላልተሰጣቸው በንጋታው አመሻሽ ላይ
እንደምንገልፅላቸው ተስማምተን ተለያየን።

ወደ ቤቴ ገብቼ ሬዲዮ ስከፍት ሬዲዮ ፋና ሰበር ዜና እያነበበ ነው።
በዜናው መዲናይቱን የማይስ ስራ መቆጣጠሉን ያበሰራል። ይሆን ተከትሎ
በአመራሮቹ ላይ ግምገማ እየተካሄደ መሆኑና በአለቱ ውሎ የአዲሳ
ፕሬዝዳንቱ አሊ አብዶ መገምገሙን ያትታል። አቶ አሊ ከተማዋ እንደ ግመ
ሽንት ወደ ኃላ እንድትጐተት ያደረገ ደንታ ቢስና ዝርክርክ መሪ እንደሆ
መሳጣባት ላይ መደረሱን ከግምግማው ቃል አቀባይ መረጃ እንዳገኙ ገለፁ።

ደንታ ቢስ!... ዝርክርክ!!

አሊን በተመለከተ ለፍሬህይወትና ሴኮ ምንም መረጃ ባልሰጠናቸ
ሁኔታ እንደዛ አይነት ዜና መለቀቁ አስገራሚ ነበር።

በንጋታው ጠዋት ረፈድ ብሎ የተጀመረው ስብሰባ በአሊ እንባ የታ
ሆነ። በእጁ የያዘው የግል ፕሬስ በርዕሰ አንቀፁ በሳለው ካርቶን ስዕል የአ
ቢሮ በራሴ ተሞልቶ፥ የሚሰራው ግራ ገብቶትና ንፍጡ ተዝረክርኮ የሚያ
ነበር። ይህም ቢሆን አስቀድሞ የተሰራ ካልሆነ በአንድ ምሽት ተዕፎ ለህትመ
አይደርስም።

አሊ በሲቃ ተሞልቶ፥

"የእኔስ ይሁን አዳው ገብስ ነው፣ ቢያንስ ለባለቤቴና ልጆቼ እንኑ
አይታሰብም? ባለቤቴ ምሽት ላይ ሀዘን ቤት ሄዳ መሳለቂያ ቢያደር
አያለቀሰች መጣች። ዛሬ ጠዋት ልጆቼ ትምህርት ቤት ቢያስጨንቋ
ደውለው ደንታ ቢስና ዝርክርክ ማለት ምን እንደሆነ ጠየቁኝ" አለ።

ካድሬው በቅንብሩና ቤተሰቦቹ ላይ በደረሰው ውርደት እዘነ አ
በአሊ አብዶ ላይ የቀረበበት ስድቦች የሚያንስበት እንደሆነ ያውቃል።
አብዶ በብዙ ጉዳዮች ወንጀለኛ ነው። ኢትዮጵያዊነት እና የጋራ ሙ
እሴቶቻችን እንዲጠፉ አድርጓል። ህዝቡ በዘር መከፋፈሉ ሳያንስ በሀይማ
ጐራ ለይቶ እንዲጫረስ ለማድረግ ቀን ከሌት የሰራው አሱ ነው። የተጣ
የንዋይ ፍቅር ለማሟላት ህገ ወጥ መስኪዶችን አስገንቢቷል። በዚህ ምክ
ብዙ ዜጐች አርስ በራስ ተጋጭተዋል። በመንግስት ታጣቂዎች ተገለ
የህዝቡ ንብረት የሆነው መሬት እንዲዘረፍ አድርጓል። ይህም ከአስር በ
አይደርስም።

በመሆኑም የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መቀየር አለበት ብሎ ሂያምን፣ ግን ደግሞ ፖሊሲ ከመለወጥ አንፃር እሱ አንዳችም ሚና ለውና ለዓሉት ሰዎች መልእክታችንን እንደሚያደርስ በቅንነት ገለፀ። ሩ ጉግር በራሱ አማራሞትን የፈጠረ ነበር። አንድ የውጭ ጉዳይ ቴር ሚንስትር በራሱ ተቋም የሚፈፀመውን ፖሊሲ ችግር አለበት ግን የመወሰን ስልጣን የለኝም ሲል ምን ሊባል ይችላል?...

ያዉም የዶክተሪ ሚኒስትር!!

የዚኑ አለት ማታ አሊ አብዶ ቢሮው ጠራኝ ። ሄድኩኝ። ለመቀመጥ ኑ እድል ሳይሰጠኝ፣

"ስድበህ ለሰዳቢ ዳረከን፣ ተቀዳ ኢህአዴግ አለመሆኑን እያወከ እንዴት ህ አይነት አስተያየት ትሰጣለህ? በዲፕሎማሲው ዙሪያ የስዩምን ከፍተት ል ተብሎ እንጂ ፀረ - ኢህአዴግ መሆኑን ጠፍቶህ ነው?" አለኝ።

ሰለ ተቀዳ እንደማላዉቅ ገለፅኩለት። ርግጥም በተባራሪ ከሚወራው ስለ ዶክተሩ የማውቀው ነገር የለኝም። የአቶ ስዩምን የብቃት ማነስ ለት እሱ እንደሆነ፣ ካለፈው ስርአት ጋር ንክኪ እንዳለው፣ ጐበዝ አማር ጪዎች እንደነበር ሲወራ ሰምቻለሁ። በፓሊሲው ላይ ልዩነት ያነሳት ሀርት ቤት የአንድ ተቋም ራዕይ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዴት ሚቀረፅ የተማርኩትን እንደሆነ ጨምሬ ነገርኩት።

አሊ ጨሰ ።

የሰነፍ ስድቡን አዘነበብኝ።

"ፖሊሲውን ያወጡት ሰዎች ያልተማሩ ይመስልሀል? ከልጅ አእምሮ የሆነ ጉዳይ ሰለዓፉ ነው ሮኬት ሳይንስ የሆነብህ!" አለኝ። ገዘም አልኩት፣ ሰው ብዬ።

ትንፉሽ ወሰዶ፣

"የምትሰማ ከሆነ ኢህአዴግ ሆኖ በድርጅቱ መርሆዎችና ፖሊሲዎች ላይ ኑ ማንሳት አይቻልም።ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ማክበር አለብህ። ነዚያ ግን ድርጅቱን ለቀህ መውጣት ይኖርብሀል" ብሎ ዘቻ አዘል ነቂያ ሰጠኝ።

ብናደድም የመጨረሻውን ድንጋይ ሳልወረውር መውጣት ስላልፈለኩ፣

"እቶ አሊ እኔ አስከሚገባኝ ፓሊሲ የሚቀረፀው ከዚህኛው አማራጭ ው ይሻላል በሚል ስሌት መሰለኝ። በመሆኑም የድርጅታችንን አማራጭ ኮማሪሪውን በእውቀት ላይ በመመስረት ብንነነዘበው የተሻለ ይመስለኛል" ት በስላቅ ተናገርኩት።

እንደወፈፌ አደረገው። ሰሜን አየጠራ፣

"ቀስ ብለህ እደግ!... አንደ ጓደኞችህ ብትበስል ይበጅሀል!" በማለት

አመናጭቆ አሰናበተኝ።

***

በንጋታው ጠዋት ዶክተር ተቀዳ በፓሊሲው ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች የያዘች አንዲት ወረቀት በተነ። ማሻሻያው በፓሊሲው ላይ የኤርትራ መንግስት በተመለከተ የተቀመጠው ሙሉ ለሙሉ ተሰርዟል ይላል። አሊን በሾኬ አየሁ ፣እሱም እያየኝ ነው። ትላንትና ዝም ያለው ካድሬ ስለማሻሻያው ትከከለኝ ለመግለፅ እጁን ችቦ አደረገ።

በምላ አረፍት በድጋሚ ቢሮው ጠራኝ። ድንቁርናውን ተጠንዝቦ ይቅር ሊጠይቀኝ እንደሆነ ገመትኩ። "ሮኬት ሳይንስ የሆነብኝ ለእኔ ነው!" የሚለኝ መሰለኝ።

የሆነው ግን ሌላ ነበር***

እኔ አሰተዳደር ዘርፍ ሆኜ በተመደብኩበት ዞን መስጥ በሚገኘው ወረ 24 አስቸኳይ ስራ ስለመጣ ስልጠናውን ማቋረጥ እንዳለብኝ ነገረኝ። ስራ እውነተኛ ኢህአዴግነቱ በወሬ ሳይሆን በተግባር የሚለካበት እንደሆ አስገነዘበኝ። ከሰአታት በኃላ ካሊድ ቢሮ ስብሰባ ሰለሚጀመር ምሳዬን በል እንድሄድ አዘዘኝ።

***

በአለ. አብዶ ቀጭን ትእዛዝ መሰረት ስልጠናውን አቋርጬ ካሊድ ቢ ተገኘሁ። ለእኔ ሳይነገረኝ በስሬ ያሉት ወረዳ 24 ሊ/መንበሯ ወይዘሮ መሰ ረሺድና በዛው ወረዳ ቀበሌ 15 (አየር ጤና) ሊ/መንበሩ ዘርመ ከማ ተገኝተዋል። አንድ የማላውቀው ፂሙን ያንፏረረ በጉልማሳ እድሜ ያለ ሰ የተጠቀሰለ ወረቀት ይዞ ተቀምጧል። ግራ የሚያጋባ ነው!

ስብሰባው በካሊድ ዲስኩር ተጀመረ። በመዲናይቱ የክርስቶ እስልምና ተከታዮች ህዝብ ብዛት፣ ቤተክርስትያኖችና መስኪዶ አለመመጣጠን፣ ይህንን ችግር የፈጠሩት ያለፉት መንግስታት እንደሆ አብዮታዊ መንግስታችን የተዛባውን ለማመጣጠን በትጋት እየሰራ እንደሆ ይህ ደግሞ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የፀና ደጋፊ የሆነውን የመሰለ ማህበረሰብ የበለጠ እያሰደሰተው እንደሄደ ተናገረ። እነሱ እንደሚ እየነቀነቁ፣ እኔ ደግሞ ተከታዮን ለመስማት በመጓጓት አዳመጥነው።

የተሰበሰብንበት ምክንያት በወረዳ 24 ቀበሌ 15 ሁለት የተለያዩ ቦታ ላይ ህጋዊ በሆነ መንገድ የመስኪድ ግንባታ ስለተፈቀደ አፈፃፀሙ ላ

ሃር እንደሆነ ገለፀልን። በስብሰባው አብረው ያሉት ጐልማሳ መሀመድ ደባልና የመስኪድ ማንባታዉ አስተባባሪ እንደሆነ ጨምሮ ተናገረ።

በአንድ ቀበሌ ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜያዮች መስኪድ ለመስራት እንዴት ሽል የሚል ጥያቄ አነሳሁ። ሰዎቹ የመስኪድ ማንባታ የጠየቁትና ሙት በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት ህግን ተከትለው እንደሆነ ሚ ገለፀ። ካቢኔው በቅድሚያ ለሚመጣ ጥያቄ ፍትሀዊነቱን እየፈተሸ ሚፈቅድ ጭምር ቆጣ ብሎ ተናገረ... እንዳለታው!

ወይዘሮ ሙለሜ በበኩሏ የመስኪድ ማንባታ ጥያቄው የአስተባባሪ ው ብቻ ሳይሆን በቀበሌው የሚኖሩ ሙስሊሞች መሆኑን የሚያሳይ ፈርማ የተሰባሰበበት ወረቀት አውጥታ አሳየች። ኮሚቴው በጠራው በአካል ተገኝታ እንዳረጋገጠች ማስተማመኛ ሰጠች።

የቀበሌው ሊቀመንበር እሱ የሚያስተዳድረው ቀበሌ ከፍተኛ ፊያ ቦታ ስለሆነ ጥያቄውን ፍትሀዊ እንደሚያደርገው ነገረን። የህዝብ ብን በጐሳና ሀይማኖት በመከፋፈል ዘረዘረ። የሀይማኖት ተቋማት ብዛት ታዊ በሆነ መልኩ እንደተሰራጨ ገለፀ።

የመጨረሻው ተናጋሪ ጐልማሳው አንጣዳ ሆነ። ሰዉየው ፍታዱን ኘት ስድስት ወር እንደፈጀባቸው፣ አንደኛውን መስኪድ ለማሰራት ቃል የአንድ አረብ ሀገር ልዑል እንደሆኑና ቃላቸውን ሳያጥፉ መፍጠን ነባቸው፣ ሁለተኛውን የሚያስገነቡት በአካባቢው መኖሪያ ቤት የሰሩ ጎጋዴዎች እንደሆኑ ተናገረ። በእጁ ያዘውን ፕላን እየዘረጋ በተጨማሪም ነቢው ለህዝቡ የሚጠቅመው መሰረተ ልማት፣ ትምህርት ቤትና ጤና ጣቢያ እንደሚገነባ ማብራሪያ ሰጠ።

እነሱ የተናገሩት እውነት ከሆነ ህበረተሰቡ ሀይማኖት ሳይለይ በጋራ ድቶ እንደሚሰራ የቀደመው ልምዶች አንዳሉ ስለማውቅ ዝምታ መረጥኩ። ሳባ ክርስትያንና ሙስሊሙ ማህበረሰብ ከመቻቻል አልፎ እርስ በራስ ዳዳ ህዝብ ነው። ደስታውን ፣ሀዘኑን፣ አውደ አመቱን በጋራ የሚያከብር ና የሚያስቀና። ቤተሰቦቻችን የአሙቱ ገበርኤልን ለመዘከር ድግስ ጋጁ ሁለት ድስት ጥደው ነው። በተመሳሳይ የረመዳንን ጾም መስሊም ሖቶቻችን ቤት ሄደን አብረናቸው እናፈጥራለን። አንደነሱ የጾሙን ወቅት ት እንጠብቃለን።

ካለድ ማንባታው እንዴት እንደሚፈፀም ዘርዘር አድርገው አቀረበ።

ዙሪያውን የማጠር ስራ ለሊት እንደሚጀመር፣ ኮሚቴዎቹ በቂ ድንጋይ፣ አሸዋ ሲምንቶ እንዳዘጋጁ፣ ከዚኑ የተውጣጡ 200 ፓሊሶች እንዲዘጋጁ ለፓሊ ኮሚሽነሩ ጥብቅ መመሪያ መስጠቱን ገለፀ። ፀረ ሰላም ሀይሎች ሊያደር የሚችሉትን ትንኮሳ የመመከት ስራ በወረዳው ፓሊስ አዛዥ ተሰፋ ፈርሻ ፣ በእኔ ላይ እንደወደቀ ነገረን።

እነሱ በገለፁት መልኩ ከሆነ ለምን እንደ ሌባ በለሊት ፣ ያው በፓሊስ ታጅበን ለመፈፀም እንፈልጋለን የሚል ጥያቄ አነሳሁ። ካለ እኩልነትን የማይወዱ ጥቂት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጠላቶች እንዳይረብ በማሰብ የታቀደ መሆኑን ነገረኝ። ካሊድ ስለ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሲና አወቅሽ-አወቅሽ ከተባለችው የቄሱ ሚስት ያስንቃል!!

ካሊድ አብዮታዊ ነበር።

***

የእነ ካሊድን ስብሰባ እንደጨረሰኩ በቀጥታ ጦር ሀይሎች ሚገኘው የኮማንደር ተሰፋ ፈርሻ ቢሮ አመራሁኝ። ኮማንደር መግናኛ ፊ ላይ ተተክሏል። ረፍት እንዳጣ ፊቱ ያስታውቃል። ሞላሸት መስዓ መምጣቴን እንዳረጋገጠ ጊዜ ማጥቃት አልፈለገም። የመጀመሪያው አፐ ለሊት ስምንት ሰአት፣ ሁለተኛው በንጋታው በተመሰላይ ጊዜ እንደሚጀ ነገረኝ። ለመጀመሪያው ቀን 100 ፓሊሶች እንደተዘጋጁና አስቀድመው ሌ ሰባት ሰአት ላይ መንገዶቹን እንደሚዘጉ፣ አስከዛው ድረስ ከወረ መከላከል ሀላፊ ውጭ ማንም ተልእኮውን እንደማያውቅ ገለፀ።

ቀድሞ መንገሩ ችግሩ ምን እንደሆነ ጠየኩት።

ኮማንደር ፊቱን ከሰከሰ፤

"ሚስጥሩ እንዳይወጣ ተፈርቶ ነው። እንደምታውቀው የህይ ነገር በጣም ስሱ ነው። መስኪድ እንዲገነባ ትእዛዝ የተሰጠባቸው ሁ ቦታዎች በጥምቀት በአል የታቦት ማደሪያ ናቸው፣ የሚቀጥለው ወር ጥ የጥምቀት በአል የሚከበርበት ስለሆነ ከፍተኛ ግጭት ሊነሳበት ይችላል ግምት አለን።" አለኝ።

"ታቦት ማደሪያ! ? ... ታቦት!?..." ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ።

"መረጃ ያለህ መስሎኝ ነበር፣ ሌላ ቦታ ቢሆን ምን አስጨነቀን ነው። ቢያንስ የጥምቀት በአል ይለፍ ብለናቸው ነበር። አሊ አብዶና እኔንና የፓሊስ ኮሚሽነሩን በፍቃዱ ቶሌራን ጠርተው ማስፈፀም ከልጅ የስራ መልቀቂያ አስገቡ ብለው አሰጠንቀቁን።" አለኝ።

***

ከኮማንደር ጋር አብረን አምሽተን ለሊት ሰባት ሰአት ሲሆን አረ

ወደሚሰጥበት ቦታ ሔድን። ቦታው በአየር ጤና ትምህርት ቤት ወደ ውስጥ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል የሚያስገባ የተንጣለለ ሜዳ ላይ ነው። ከሜዳው ፊት ለፊት የኪዳነ ምህረት ቤተክርስትያን ይታያል። ቦታው ቤተክርስትያኗ በጥምቀት በአል ታቦት የምታሳዳርበት ቦታ ነው። 100 ፓሊሶች በአምስት ቡድን ተከፍለው በሜዳው ዳር ተቀምጠዋል። ግራ መጋባት ይታይባቸዋል። በአካባቢው ህገ ወጥ ማንባታ የማፍረስ ስራ በየጊዜው ስለሚከናወን ለዛ የሚታዘዙ እንደሆነ በሹክሹክታ ይነጋገራሉ። አንዳንዶቹ የወታደር አጥሪት ስለተከሰተ ባድመ ሊልኩን ነው ብለው ሲቀላለዱ ሰማኋቸው።

ኮማንደር ተሰቃ በየቡድኑ እየዞረ አረንቴሽን ሰጠ። እያንዳንዱ ቡድን ወደ ሜዳው የሚያስገቡ አምስት መንገዶችን እንደሚዘጋ፣ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ መውጣታቸውን ከማዕከል ካልተነገረ በስተቀር እንድም ጥይት እንዳይተኮስ፣ ምግብን ጨምሮ ሌሎች ሎጅስቲክ በተመደቡበት ቦታ እንደሚከፉፈልና ማንም ከምድብ ቦታ መንቀሳቀስ እንደማይቻል ትእዛዝ ሰጠ... ጥያቄ የሌለው ፓሊሳዊ ትእዛዝ!

ኦፕሬሽኑ ተጀመረ።

የቡና ነጋዴዎች ከተባሉት ግለሰቦች ቤት ውስጥ ድንጋይና እሸዋ ሞልተው የቆሙ ከ10 በላይ የጭነት መኪናዎች ተግተልትለው የጫኑትን አራገፉ። በየቤቱ ተደብቆ የነበረው ማንበኞችና ቀን ሰራተኛ ከፓሊሱ ቁጥር በላይ ሆኖ ተዘረገፈ። የአጥር ማንባታው በአምስቱም መንገዶች ዙሪያ ተጀመረ። ሰጠጠር መጣያ እስከሚቸግር ድረስ ሜዳው በወጣት ሙስሊሞች ተጥለቀለቀ። ዘግየት ብለን እንዳጣራነው አብዛኞቹ ወጣቶች የአካቢው ነዋሪዎች አልነበሩም። ከአዲሳአባ ዩንቨርስቲ፣ሀንጻ ኮሌጅ፣ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ፣ ከመርካቶ፣ አጠና ተራ ... የመጡ ናቸው።

www.

ከንጋታው አስራ ሁለት ሰአት፡

ከኪዳነ ምህረት ይሰማ የነበረው ቅዳሴ ተጠረጠ። ከቤተክርስትያኑ የድረሱልኝ ጥሪ ተሰተጋባ። የድምፅ ማጉያው የአሉታ ድምፅ ደጋግሞ አሰማ። የአካባቢው ነዋሪ ቤተክርስትያኒቱ ላይ አደጋ ደረሰ በማለት ሊታደጓት መሯሯጥ ጀመሩ ...ወጣቱ፣ አዛውንቱ፣ ከርስትያኑ፣ ሙስሊሙ። ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ቀረብ ብዬ ቆምኩ። ቄሱ በማይክራፎን ህዝቡን የሚያነሳሳ ንግግር እያደረጉ ነበር። መንግስት ፓሊስ አሰማርቶ የጥምቀት ማደሪያውን ለባለሀብት እያከፋፈለ እንደሆነ ይናገራሉ። አጠገቤ የዛፍ ዝንጣይ የያዙ አዛውንት ለየት ስላሉብኝ ምን እንደተፈጠረ ጠየኳቸው። ዝንጣፊውን እየጣሉ፤

"አሳት የተነሳ መስሎኝ ነበር። ከቄሱ እንደሰማሁት የጥምቀት

ማደሪያውን መንግስት ለባለሀብት አየሸጠው ነው። ይሉኝ መንግስት ግን ምን ነክቶታል? እኔ እዚህ አካባቢ ከኖርኩ ከአስር አመት በላይ ሆኖኛል፣ ፓሊሶቹ አሁን የከበቡት ቦታ በየአመቱ የጥምቀት ማደሪያ እንደሆነ አውቃለሁ። እኔ በእምነቱ ሙስሊም ነኝ። ነገር ግን የሀይማኖት ቦታዎች መከበር አለባቸው።" አሉኝ።

"እባቴ! እኔ እንኳን የሰማሁት ለመስኪድ ሲሰጥ እንደሆነ ነው።" አልኳቸው፣ ስሜታቸውን ለማየት ፈልጌ።

"ተሳስተሀል ወንድሜ! ይህ በፍፅም የማሆን አይደለም፣ ሙስሊሙንና ከርስትያኑን ለማቃቃር ካልታሰበ በስተቀር። እኔ አካባቢውን ወክዬ የወረዳው አስልምና ምክርቤት አባል ነኝ። የመስኪድ ግንባታ ጥያቄ ያቀረብነው ትምህርት ቤቱን ተሻግረህ ባለው ከፍት ቦታ ላይ ነው፣የከርስትያን ወንድሞቻችንን ድጋፍ አግኝተናል።

ከሰውየው ጋር እያወራሁ ሲቪል የለበሰ ፓሊስ ወደ ጆሮዬ አንሸካሸከ። ሁኔታዎች እየተባባሱ መምጣታቸውን፣ ነዋሪው ስለት ያላቸው ነገሮች ይዞ መውጣት መጀመሩን ፣መንግስት መሳሪያ ያስታጠቃቸው ሚሊሻዎች ከህዝቡ ጋር እንደተሰለፉ ነገረኝ። የቤተክርስትያኑን ሙቢራትና ስልክ እንደቆረጡትና ደውሉን ለጊዜው እንደተቆጣጠሩት ገለፀልኝ። በስውር ፓሊሶች ታጅቤ ወደ ግንባታ የሚካሄድበት ቦታ ሄድኩኝ።

***

ጠዋት አንድ ሰአት፡

በአጥሩ አየታጠረ ባለበት ቦታ ያሉ ወጣትና አዛውንቶች አምላካቸውን መንግስትን ያመስግናሉ። ይዘምራሉ። ግንባታውን ለማፋጠን የሚሰሰት ጉልበት የላቸውም። ብዙዎቹ በደስታ ሰክረዋል። ጥቦቶች በየቦታው እየታረዱ ነው። ሴቶቹ የምጣድ ጥብስ ለቁርስ ለማድረስ ይንደፋደፋሉ። ሰርግና ምላሽ ሆኗል።

በዙሪያው ደማሞ አሉታውና የድንጋይ ኩርምታው መራሃ አንቀጥቅጧል። _ከየመንደሩ የሚወረወሩት በአሸዋና ጋዝ የተሞሉ ላስቲክ ኳሶች ሲፈነዱ የሚያስመት ደምፅ ቦታውን የጦርነት ቀጠና አስመስሎታል ጉዳቶች መስማት ጀምረዋል፣ ጊዜያዊ ማዘጋጃ ላይ ያለችው የኮማንደር መሃ ሬዲዮ ቆታ አጥታለች።

"ዋልያ 24! ኑበር 24 ነኝ... እኔ ባለሁበት አካባቢ ሁለት እባ ከባድ ጉዳት ደርሶባቸዋል።"

"ዋልያ 24! አንበሳ 22 ነኝ... እኔ ባለሁበት አካባቢ አምስት አባ ተጐድተዋል እርዳታ ይፈልጋሉ"

"ዋልያ 24! ዋልያ 23 ነኝ... ከቤተክርስትያኑ መገሙር እያሰ

እንደጉርፍ እየመጡብን ነው... ሀይል ይጨመርልን"

ኮማንደር በዋልያ 23 ተናዶ ምንም ኃይል እንደማይጨመርለት ስለሰለት፣ "ዘላለሙን እንደፊራ ይኖራል" ብሎ ለራሱ ተናገረ። ማን እንደሆነ ሰየኩት። የወረዳ 23 ፖሊስ አዛዥ የነበረው ጥሩነህ በርታ እንደሆነ ነገረኝ...

(ኮማንደር ጥሩነህ በዞን በሚካሄደው ግምግማ ሁልጊዜ በስንፍናው ይወቀስ ነበር። ኢህአዴግ ውስጥ ከችሎታ ይልቅ የሚዘረጋ የጥቅም ኔትወርክ ውሳኝ በመሆኑ ከደቡብ ጀምሮ ከገቢዎች ሀላፊ ከነበረው ጉበረዋህድ ጋር በዘረጋው ሰንሰለት መሰረት ኮማንደርነቱን ትቶ በተራ ሰራተኝነት ወደ ጉምሩክ እንዲዘዋወር አደረገው። እኔም ታታሪ ነው ብዬ የድጋፍ ደብዳቤ ፃፍኩለት። የቢና ጉምሩክ ካድሬዎች አስር ውስጥ የጉበረዋህድን ስም ስሰማ ጥሩነህ እንደሚኖሮ ለሰከንድ አልተጠራጠርኩም ነበር። የቄራና ገቦ ህዝብም ፊት ለፊቴ ተደቀኑ፣ በምርጫ 97 ጉበረዋህድን በእነዚህ አካባቢዎች ለፓርላማ እንዲወዳደር አቅርበነው ነበር። የአካባቢው ህዝብና ጉምሩክ የሚሰሩ ሰራተኞች ለመስማት የሚዘገንኑ ጥቆማዎችን ይዘው ወደ እኛ መጡ። በመረጃ አስደግፈን ለአለቃችን ከንቲባ አርከበ አቁባይ አቀረብንለት። አርከበ "የትግራይ ጠላት የሆነው የቅንጅት ወሬ ነው" ብሎ አጣጣለብን።

እውነት ይዘገያል እንጂ...

ጉበረዋህድ ወደ ወህኒ ወረደ። ኮማንደር ጥሩነህንም አጀበው። ከዛ ቀን ጀምሮ ለጉበረዋህድ ሀገሪቷ ወዴት እየሄደች እንደሆነ ተገለፀለት። ሁለቱም የቅርብ ጓደኞቼ ነበሩና ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ ፍትህ ለነበሳቸው ደግሞ መፅናናት ይሁን!)

***

ሁለት ሰአት...

ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ ሄዱ። እናቶች ነጠላቸውን ታጥቀው ደረት ይደልቃሉ። ወጣት ሴቶች ከፖሊስ ጋር ከፈለከ ግደለኝ በሚል ፀጉራቸውን እየነጨ ይተናነቃሉ፣ ብዙዎቹ ባዶ እግራቸውን ናቸው። ጐረምሳ ወጣቶች የድንጋይ ናዳ ያዘንባሉ።

መሳሪያ ለመንጠቅ በተደረገ ትንቅንቅ አንዲት ሴት በጥይት እግሯ ላይ ተመታ ቆሰለች። ሁለት ፖሊሶች በከባድ ሁኔታ ተጐድተው ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ተወሰዱ። ጥይት መቆላት ጀመረ።

ለሁለተኛው ግንባታ ያስቀመጥናቸውን ፣00 ፖሊሶች አመጣናቸው። በየበድኑ ተደለደሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ የፖሊሶቹ ሁኔታ ራሱን የቻለ ትራጀዲ

ነበር። ከህዝቡ ጋር እያለቀሱ በሚወረወርባቸው ድንጋይ ይደበደባሉ፤ ሲብስባቸው ወደ ላይ ይተኩሳሉ። ብዙዎቹ በወረዳው ተወልደው ያደጉ በመሆኑ ከነዋሪው ጋር ቤተሰብና ጐረቤት ናቸው... ወንድምና እህት፤ ልጅና አባት ውስጣቸው አንድ ሆኖ የሚጨቍጨቅበት ቦታ+++ አየር ጤና +++የደም መሬት!

+++

በአየር ጤና አየሆነ ያለውን ለካዛንቺሱ ስውር መንግስት ካድሬ ለሆነው ለፍስሀ መለሲ ደውዬ ነገርኩት። እነ አሊ አብዶ የቀረቡላቸውን የተሳሳተ መረጃ ነገረኝ። ግብር የማይከፍል ገበሬ መሬቱን እንደሚያርሰው፤ በእካባቢው የኢህአዴግ ደጋፊ የሆኑ ሙስሊሞች በሰፈው መስፈራቸውን እንዳስረዳ ገለፀልኝ። እነ አሊ ባህታዊውን እያታለሉት እንደሆነ አስረዳኝ። የተጀመረው ግንባታ ማሰቆሙ ችግር ስለሚያመጣ እንዲቀጥል፤ ሁለተኛውን ግን እሱ ምላሽ እስኪሰጠኝ ድረስ እንዳላስፈፅምና ከማንም ጋር እንዳልነጋገር አስጠነቀቀኝ።

ብዙም ሳይቆይ ካሊድ ደወለልኝ። በአንድ ቀን ሁለቱም ማስፈፀም እንደማንችል ነገርኩት። የስድብ ውርጅቡኝ አወረደ። አብዮታዊነት መጓደሉ የህይማኖት እኩልነትን አለመቀበል ቁልፍ ችግሬ እንደሆነ ገለፀ። እኔም ጀርባዬን ተማምኜ ሰለነበር ለእንደዚህ አይነት ስራ አስተዳደር መሆን እንደማልፈልግ ለካዛንቺሱ መንግስት መልቀቂያ አስገብቼ ወደ ቀድሞ ስራዬ እንደምመለስ ነገርኩት። መጨረሻዬ ከርቸሌ እንደሚሆን እየደነፋ ሲፎህ "ካሊድ! ማን ሳ
አግረ መሞት እንደሚታሰር በሂደት እናየዋለን" አልኩት+++
ፍስሀ የአህያ ባል እንደማይሆንብኝ ተማምኜ!

ቃለ ምልልሳችንን ሲያጓጉጥ የነበረው ኮማንደር ተስፉ ፈርሻ ጠጋ ብ
እንዲህ አለኝ፣

"እነዚህን ሰዎች ተጠንቀቅ። ስውር ተልእኮ እንግበዋል። በያዝ
አመት ብቻ በእኛ ወረዳ ከ10 በላይ መስኪዶች አስገንብተዋል። ማስፋፊያ
ትኩረታቸው ነው። በተለይም አየር ጤና፣ ቀራንዮ፣ አጠና ተራ፣ ከእኔ
ጀርባ ጅማ ሰፈር የሚጠቀሱ ናቸው። ተከታትለን እንደደረስንበት ከሆነ የ
ሰፈሮቹን የመስኪድ ግንባታ የምታስተባብረው በዛ አካባቢ የምትኖረው
አብዶ እህት ናት። አሊ አብዶ አሷ ቤት ኖሮ ያውቃል። በቅርብ ቀን ከ
መስኪድ 500 ሜትር ርቀት ላይ የግለሰብ ቤት በመግዛት መስኪድ መሰረ
ነበር። በምርጫ 92 ኢዴአፓን ወክሎ ለፓርላማ የተወዳደረው አበበ
ህዝቡን አስተባብሮ የሰቀሉትን ጨረቃ አስወረደ። እንደምታውቀው አሊ
ከሚፈራቸው ሰዎች አንዱ አበበ ቀስኖ ነው።"

ኮማንደር ቀጠለ፤

"... ለአለ, አብዶ ከአረብ ሀገር የሚመጣው ገንዘብ የሚያልፈው በእሁቱ እማክኘነት ነው። ቤቱን የሰራው በዛ ገንዘብ እንደሆነ ይታማናል። የእሁቱም ህይወት በማይገመት ደረጃ ተለውጧል። በአካባቢው ተወልዶ ያደገው አበበ ክፉ ውስጠ ሚስጥሩን ያውቃል። አቤቲ ድረስ በመሄድ አስፈራርቷታል።"

***

ከረፉዱ ሶስት ሰአት:

ፓሊስ የቤተክርስትያኗን ቁሶችና የአመፅ አስተባባሪዎችን እየለየ ማሰር ጀመረ። የደብሩ አስተዳደሮችና ቁሶችን በአቅራቢያው ወደሚገኘው ወረዳ 23 ፓሊስ ጣቢያ ተወሰዱ። እያስቸገሩ ያሉትን ሴቶች ወደ ዞን ፓሊስ ተጋዙ። እፍታም ሳንቆይ አየር ጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በረበሻ ተናወጠ። መኪኖች፣ መቀመጫ ዴስኮችና አንፓሎች ተሰባበሩ። ተማሪዎች ወደ ከፍል እንገባም በማለት ሜዳ ላይ ተዘረገፉ። ፓሊስ ዙሪያውን ከበበ። ይቺ የጭንቅ ሰአት እንድታጥር ተመኘሁ።

***

የመስኪዱ አጥር ግንባታ በብርሀን ፍጥነት ተጓዘ። በነፃ የሚያግዙት ወጣቶች የስራ ትጋት እስከ ምሽት አልቀነሰም፣ መዝመራቸው የፍንዳታውን ድምፅ ሸፍኖታል፣ ድግሱም አልበረደም። ከምሽቱ አምስት ሰአት አካባቢ አራት የግል ታርጋ ያላቸው ላንድክሩዘር መኪናዎች አጥሩን አልፈው ወደ ውስጥ ገቡ። ከመጀመሪያው መኪና ውስጥ የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ዶክተር መሀመድና በካሊድ ቢሮ አብሮን የተሰበሰበው የማንባታ አስተባባሪ ወጡ። ከሁለተኛው መኪና የአረብ ሀገር ዜጐች የሚመስሉና ጥምጣም ያደረጉ ሰዎች ተከታትለው ወጡ። ከሶስተኛው በኢጃብ የተሸፈኑ ሶስት ደርባባ ሴቶች። ሰባቱም ከኋላ ተሰልፈዋል።

በስራ ተጠምደው የዋሉት ወጣቶች በዝማሬና ለአምላካቸው በሚያቀርቡት ምስጋና ደማቅ እቀባበል አደረገላቸው። ወጣቶቹ አስቀድሞ መረጃ እንደነበራቸው ያስታውቃል። የመስኪድ ማንባታ አስተባባሪው እየመራቸው ወደ እኔና ኮማንደር ይዟቸው መጣ... ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሰላምታ እየሰጠን አጠር ያለ ስብሰባ እንድናደርግ መምጣቱን ነገረኝ። አጅበውት የመጡት ሰዎች ከኋላው ቆመዋል። ..."ማን ልበል አላወኩትም?" አልኩት፤ ሆን ብዬ ...

"የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንቱ የተከበሩ ዶክተር መሀመድ ናቸው?..." ባሉ አስተባባሪው ተናገረ።

"የኦሮሚያ አስተዳደር ምን አማብቶት ለስብሰባ እንደመጣ አልገባኝም ሁሉም እንዲሰማ ፎክ ብዬ ተናገርኩ።

"የምናግዛችሁ ነገር ካለ ብለን ነው፣ ወረዳው ከኦሮሚያ ስለሚዛ ድጋፍ ልንሰጣችሁ ስለፈለግን ነው።" ዶክተሩ ቀስ ብሎ ተናገረ።

"አያስፈልገንም። ራሳችን የምንቆጣጠረው በቂ ሀይል አለን።" ጠ ሰጠሠት።

አስተባባሪው ስሜን እየጠራ፣

"ለሊት ለምትጀምሩት ሁለተኛው ግንባታ ተጨማሪ ሀ ያስፈልጋችኃል፣ የኦሮሚያ ፓሊሶች የአዲሳባ ዩኒፎርም ለብሰው ሊቀላቀሏ ይችላሉ ብለን ነው... ከቡር ፕሬዝዳንቱ ሊተባበሯቹህ ፍቃደኛ ናቸው" በማ በድጋሚ ገለፀ።

ወደ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ዞሬ፣

"ሁለተኛው ግንባታ ከኢህአዴግ ቢሮ መልሰ እስከናገኝ አይጀመር በዚህም ላይ ቢሆን ምርመራ እየተካሄደ ነው፣ ባልጠፉ ቦታ በጥም ማደሪያ ላይ መስኪድ እንዲገነባ መፍቀድ ምክንያቱ መጣራት ይኖርበታ በውሳኔው ልዩነት ካለህ ለከተማዋ ኢህአዴግ ቢሮ መደወል ትችላለህ። "ሪ አድርጌ ነገርኩት። የእህዴድ ካድሬዎች ማን ሲጠራ እንደሚያስፈራቸ እንደሚበራገጉ ስለማውቅ።

"እዛ የሚያደርስ አይደለም።" ተሰናብቶን ከምሸሸ ብሎ ሄደ።

ዘግየት ብለን ባደረግነው ማጣራት ዶክተሩን የላከው በወቅቱ የኦሮ ፕሬዝዳንት የነበረው ጁነዲን ሳዶ እንደነበረ አረጋገጥን። ዶክተሩ ብዙ ጊዜ የሚያጠፉው እንደዚህ አይነት ሰራዎችን ፊት ለፊት ወጥቶ በማስተ እንደሆነ ደረስንበት፣ ሰውየው ፅንፈኛ አመለካከቱን በግላጭ የሚያቀርብ፣ አ ተርፎም ኦሮሞነትና እስልምና የአንድ ሳንቲም ግልባጭ ናቸው የሚል እ ቅስቀሳ እንደሚያደርግ በከትትል ደረሰንበት።

እነ ጁነዲና አሊ አብዶ ደግሞ መኖሪያ ሀንፃቸውን ኢያስገነቡ ያ በግንባታ ኮሚቴው አሰፈፃሚነት ከአረብ ሀገራት በሚላከለቸው ገንዘብ መ ተረጋገጠ። ከአለታት በአንዱ ቀን በምሰራበት ዞን የገቢዎች ምክትል ሀ የነበረችውን አስቱ ፈንቴ (የበረከት ስምኦን ሚስት) ቢሮዬ ጠርቼ በገ ነገርኳት። አስቱ ልታይ የማታበዛ፣ ሰልጣን የምትሸሽ፣ ጨዋና ትጉህ ሰራ ነበረች። እንደ አውነቱ ከሆነ ከአቶ መለስ ቡተቃራኒ የበረከትን አ የቀጠለችለት አስቱ ናት። አሱም ቢሆን በየደቂቃው "አሲ!" እያለ ስል ያስጨንቃል። ውጭ ሀገር እንኳን ሲሄድ ግራ ገኑን ይዞ ነው።

ዶክተር መሀመድን አስመልከቼ የነገርኳትን በጥሞና ሰታዳምጠኝ ቆ "ቆይ ዝምበል!" ብላኝ ወጣች። ከወራት በኋላ ዶክተሩ ከምክ ፕሬዝዳንትነትና አህዴድ አባልነት ተባረረ። ጠቡበነትና ጽንፈኝነት የ

ማዕደግ ተጨመረለት። በተራዬ አሰፉ ቢሮ ሒጂ እጅ በመንሳት ምስጋና አቀረብኩ።

***

በሳምንት ውስጥ የአየር ጤና መስኪድ አጥርና ጊዚያዊ የቆርቆሮ ቤት ታነጉብኝ ተጠናቀቀ። ሁለተኛው ግንባታ እስኪጣራ ድረስ በካዘንችሁ መንግስት ትእዛዝ ተቋረጠ። ህዝበ ክርስቲያኑ በበኩሉ ለጥምቀት አመፅ ቀጠሮ ይዞ አደብ ገዛ። እኛ ደግሞ የአሊ አብዶ የጨለማ ዘመን አካል ነንና ወደ ሌላ አጣፋቶ መጥቃት ተሸጋገርን።

ካሊድ ቢሮ እኔ፣ ኮሚሽነር በፍታዱ ቶሌራ፣ ኮማንደር ተሰማ፣ ኮማንደር ተስፉ በጠዋት ተገኝተናል። የወረዳ 24 የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዩ ህዝብ በእልህ ተነሳስቶ ሁለት ቦታዎች ላይ ህገ ወጥ ቤተክርስትያን በሰበት ቀን ገንብቶና ታቦት አስገብቶ አምልኮ ጀምሯል። ካሊድ ቢሮ ይተሰባሰብን ባለስልጣናት ቤተክርስትያኖቹን እንዴት እንደምናፈርስ አየተነጋገርን ነው። የተለመደው የካሊድ አብዮታዊ ደሞክራሲ ኪኒን ሽፉኑን ሰይተይር ህገወጥነትን ለመከላከል ፍቱን መዳኒት ሆኖ ቀርቧል። አዲሱ ነገር የምክትል ፕሬዝዳንቱ ደላለኝ ሽሹ መጣናት ብቻ ነው።

ህገ ወጥነት ላይ ጠንካራ እጁም ስለነበረኝ ከማስተር ፕላኑ ጋር ተመሳከሮ ወደ ህጋዊ መስመር የሚመጣበት ካልሆነም የማፍረስ ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት አስተያየት ሰጠሁ። አስቀድሞ በህዝቡ ዘንድ የማሳመን ስራ መስራት እንደሚገባ እና የሃይማኖቱን ከበር በማይነካ መልኩ መፈፀም እንዳለበት አሳሰብኩኝ። ካሊድ ተልእኮን ለመፈፀም መፍራትና ህዝበኝነት የሚል መሸከም የማልችላቸው ስሞች ጨመረልኝ... እያልቅበት!

የማፍረሱ ስራ ዛሬውኑ መሆን እንዳለበት ካቢኔው መወሰኑን ነገረን። ደሳለኝ ሽሹ በካሊድ ንግግርና በእነ አሊ አብዶ ውሳኔ ደስተኛ እንዳልሆነ ያስታውቃል። አፉ በልጓም የታሰረ አሰኪመስል ድረስ ትንፍሽ አላለም። ካሊድ ላይ ያለውን ጥላቻ አይኖቹ መደበቅ አልቻሉም። ስብሰባው አልቆ ወደ ደጅ ሰንወጣ ቢታላቅ ወንድም በሚመስል አይኑ እያየኝ፣

"እይዞህ! ሁሉም ያልቃል።" አለኝ። ደሳለኝ ጥሩ ሰው ነበር።

ሌላ የጭንቀት ሳምንት... ድቅድቅ ጨለማ...

***

ከኮማንደር ተስፉ ጋር ተያይዘን ወደ ወረዳ 24 ሔድን። ዝርዝር መረጃዎቹን ወሰድን። ቤተክርስትያኖቹ የተገነቡት ማሊፎኒ (በተለምዶ ህዝቡ ሙስና ሰፊር)ከሚላቸው ቦታዎች እና ቻይና ኤምባሲ ጀርባ ከምፒንሳቶ

እንጨት መሰንጠቂያ አጠገብ ነበር። የመጀመሪያዉ ለህይማኖት ተቋም የማይሆን ቦታ በመሆኑ ማፍረሱ እማራጭ እንደሌለው ተስማማን። ሁለተኛው ከማስተር ፕላኑ ጋር የማይጋጭና ጫካ ውስጥ ስለሆነ ወደ ህጋዊ መስመር የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባን ተማመንን።

የሚሊፎኒ ግንባታ ኮሚቴዎችን ጠርተን አናገርናቸው። መግባባት ላይ መድረስ አልተቻለም። እንደምናፈርሰው በግልፅ ነገርናቸው። ህገወጥ መሆኑን እያመኑ ቁከከራቸው እነ አሊ አብዶ ከዘረገት ህገወጥ ኔትወርክ ጋር ሆነ። እኛም ከግለሰብ እምነታችን ተነስተን እንድንደግፋቸው ያግባቡን ጀመር። የሚሆን አልነበረም፣ የሶማ የበላይነት ሌላው ስለጣሰ እኛም ማክበር የለብንም የሚባል አመክንዮ እንደማይሰራ በግልጽ ነገርናቸው። ለሚከሰተው ጥፋት ሀላፊነቱን እንደሚወስዱ አስጠነቀቅን። እንደማያዛልቅ ስንገነዘብ እነሱ በወረዳው እገዛ ተደርጉባቸው ቤተ ክርስትያኑ ፈረሰ።

የፓሊስ መኪና በሙሉ አይናችን ለማየት እንኳን የማንደፍረው ታቦት ተሸክሞ ወደ ጣቢያ መጣ። ከሌላ እሳዛኝ ድራማ ጋር ተገጣጠምኩ።

የመሣናኛ ራዲዮ ላይ የተቀመጡት ሴት ፓሊሶች ሰውነታቸው ይርዳቸ ይጮሀሉ። አንዲት አብሮ አደጌ የሆነች የፓሊስ አባል ተዝለፍልፋ አግሬ ሰ ወደቀች። አቀፍሰን አነሳናት። ለቅሶዋና መንቀጥቀጧ አላባራ ሲል ወደ በ ሸኘናት። ብዙም ሳትቆይ ስራዋን ጥላ ወደ አረብ ሀገር እንደተሰደደች ሰማሁ የእኖ መለስ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ከፓሊስነት ይልቅ አረብ ሀገር የቤት ሰራተኛ የሚያስንቅባት ሆናለች። ብሄራዊ ውርደታችን እዚህ ደረጃ ደርሷል።

ኮማንደር ግበታዊ በሆነ ሁኔታ መለየውን አውልቆ በመመር ተንበረከከ። ፀጉሩን እየነጨ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። የኮሚቴው አባ ተጅሩጠው ከተንበረከከበት አነሱት። እቢራ የለበሰውን ሱሪ በእሽ እየጠረጉ አጽናኑት።

በጥላቻና ባንዳነት ሲፈርጁን አልፎ ተርፎም በፔትሮሊየም ያ የተደለልን አድርገው ሲሰድቡን የነበሩት የኮሚቴው አባላት ተደናገ ጭንቀታችንን ተጋሩት። አብረውን አዘኑ። የነባንቡትን አጣብቂኝ በመገ ነዋሪውን ለማረጋጋት ሀላፊነት ወሰዱ። አመስግነን ሸኘናቸው። ወደ ዘ ተመለስ።

ኮማንደር መዕናኛት አቃተው። በዛ ሁኔታ እያለ ጥዬው ለ አልፈለኩም።

(ኮማንደር ተስፉ ፈርሻ ወልቂጤ ካፈራቻቸው ቆፍጣና መታደሮች አንዱ ነው፣ መታደራዊ ዲስፕልን ከተማሂላ ቁመና ጋር የተቸረ። የተነሸጠውን ቀልጦ ሲፈልም በልበ ሙሉነትና የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ያገኘውን ሰብአዊ መብቶች በማክበር ነበር። በቅርብ የምናውቀው አለቆቹ ከባድ ሰራ ከመጣብን ለይናችን የሚያርፈው አሱ ላይ ነበር። በከተማዋ የሚገኙ የፓሊስ አባላት ሽክሽክ ቢያውቁትም በአስገምጋሚ ድምፅ ይለዩታል። ኮማንደር በመገናኛ ሬዲዮ ለናንተ ምድብ ቢታቸውን የለቀቁ የፓሊስ አባላት ይሯሯጣሉ። ላልሰሙትም እንዘክሳው አጋስቷል! ዛሬ የዞኑ ተረኛ አሱ ነው" የሚል የተጠንቀቅ መልእክት ያስተላልፉሉ።)

ከብዙ ዝምታ በኃላ ወጣ ብለን ብስጭታችንን በቢራ ጠርሙስ እንድናወራርድ ጠየኩት። የመረጃ ክፍል ኢንስፔክተሩን ጠርቶ አዲስ ነገር እንዳለ ጠየቀው። በነበሰ ማጥቃት ተጠርጥሮ ለሁለት ሳምንት ከትትል ቢደረግበት የነበረው ሰው በቁጥጥር ስር እንዳዋሉት ነገረው። ወደ ማእከል ከመላኩ በፊት የተቀበሉትን ቃል እንዲያመጣለት አዘዘው።

የሀገሬ ፓሊስ ባለመሆኔ አምላኬን አመሰገንኩ። በሀቅና ታማኝነት ለሚሰራ አስር ቤት የሆነች ሀገር። ኮማንደር ተስፉ የግለሰብ ቤት ኪራይ መክፈል ከብዶት ባለ አንድ ክፍል የቀበሌ ቤት ጅማ ሰፈር የሰጠነው እኛ ነን።

ኢንስፔክተሩ ቃል የተቀበለበትን መዝገብ ይዞለት መጣ። በእርምጃ ካንበበ በኃላ ተጠርጣሪውን አናግሮት እስኪመጣ እንድታገሰው ጠየቀኝ። አብሬው መሄድ እንደምፈልግ ነገርኩት። የማስገደድ ያህል ተጫንኩት። ሀሳቡን ሰውጦ አስረኛው ወደ ቢሮው እንዲመጣ አደረገው።

በፍጹም ያልጠበኩት ነበር...

የመዲናይቱ ነዋሪ "ቀምጪ" ብሎ ከሚጠራቸው ሰዎች አንዱ በሁለት ፓሊሶች ታጅቦ ገባ። እጁ በካቴና የፊጥኝ ታስሯል። አንደ መረብ በተጠላለፈ ክር የተጠቀመ ቁምጣ ና በተለምዶ "ንጭም አዘነ" ተብሎ የሚጠራውን ነጠላ ሰበቧል። በጉማ የተሰራ በረባሶ ተጫምቷል። መረጋጋቱ እንኳን በነበሰ ማጥቃት ዶሮ የታሰረችበት ገመድ በመስረቅ የተጠረጠረ አይመስልም።

ኮማንደር ካቴናውን አስፈትቶ የሰጠውን ቃል እያመሳከረ በድጋሚ መጠየቅ ጀመረ። ከተለመዱት የፓሊስ ጥያቄዎች ተሻግሮ የሚያቀርብለት ሁልቢን ሳበው። እንዲህ በማለት ጀመረ፤

"ስንት ቁምጣ ነው ያደረከው?"

"ከውስጥ ግልገሷ ውጭ እንዲት ናት ጌታው! "

"እውነቱን ተናገር!" ኮማንደር አስገመገመ።

"ሁለት ነው ጌታው!"

"አንዱ የማን ነው?"

"የአሱ (ሚቾ) ነው ጌታው!"

"በእጅህ ላይ ንብረት፣ ገንዘብ አለ?" እንደገና ጠየቀው።

"አረ ! ምንም የለም ጌታው። በቀን በላ የምኖር ነኝ።"

ኮማንደር ተናደደ። ፓሊሶቹ ጓንት እና መቀስ ይዘው እንዲመ እዘዛቸው። ተጠርጣሪውን ሌላ ከፍል መስደው ቁምጣዎቹን አስወለቀው ፣ አልብሰውት እንዲመጡ ነገራቸው። ይዘውት ሲመጡ ሚች ራቁቱን ወ ውስጥ ተጥሎ መግኖቱን ነገረኝ።

መጨረሻውን ለማወቅ ጓጓሁ...

ፓሊሶቹ የመጀመሪያው ቁምጣ የተጠቀመበትን ከሮች በመ መበጣጠስ ጀመሩ። እያንዳንዱ አራት መአዘን ከር በተፈታ ቁጥር በቁመ የተከማቹ ባለ መቶ ብር ኖት ይዘረገፉል። ከአንዱ ቁምጣ ብቻ አስር ሺህ · ተቆጠረ።

የማየውን ማመን አቃተኝ። ከሁለት የተሰፉ ቁምጣዎች ሀያ አም ሺህ ብር ተገኘ። በቁምጣዎቹ የተደበቀው የኖቶች ብዛትና ተባዩ መሳ ለ ነበር።

"እንዴት ይሄ ሁሉ ገንዘብ ሊኖረው ቻለ ?" ስል ኮማንደርን ጠየኩ መልስ ሳይሰጠኝ ወደ ሌሎች ጥያቄዎች ተሸጋገረ፤

"የምትኖረው የት ነው? ማደሪያህን ጨምረህ ንገረኝ?"

"አለም ባንክ አካባቢ። ያላለቁ ቤቶች እየጠበኩ።"

"ስንት ቤት ትጠብቃለህ? ምን ያህል ይከፍሉሀል?"

"ሰስት ናቸው ጌታው። በቀን አስር ብር ይከፍሉኛል" ኮማንደር በ ወረቀት ላይ ሰላሳ ቁጥር ጻፈ።

"የቀን ስራ የምትሰራው የት ነው?" ሲል ጠየቀው።

"ቃሊቲ፣ አቃቂ፣ ላፍቶ፣ በሌ አካባቢ።"

"ወደ ስራ ስትሄድና ስትመለስ ምን ታደርጋለህ?"

"እንዲዘከሩኝ አየጠየኩና እየለመንኩ እሄዳለሁ ጌታው።"

"ያገኘኸውን ምግብ ምን ታደርገዋለህ?

"ሰስት ቁጥር ማዞሪያና እቡነ አረጋይ አካባቢ እሸጠዋለሁ? በርካሽ ስለምሸጥ ቋሚ ደንበኞች አሉኝ። ከሰዎች የተረፈው ለከብቶቻቸው የሚገ አሉ።"

ደነገጥኩኝ።

የነዋሪው በችጋር መመታት በዚህ ደረጃ መድረሱ። የእኔ ቢጤ ለ ያገኘውን ምግብ ተሻምቶ የሚገዛ ህዝብ። ለነገሩ ምን ይገርማል? መሀል መር ጉርሻ ይሸጥ የለ። እጅ ሞላ ያለ አንድ ብር፣ እጅ ጐደሎ ደግሞ ሀምሳ ሳንቲ ...የሁለት ምርጫዎች ወግ "የአፍሪካ ነብር!" ብሎ የሰየመሽ አዲሲቷ ኢትዮ የት ነው ያለሽው? ይህን ውርደት ሰምተሽ ይሆን? ...የሙሴን በትር የያዘ መልአከ የት ነው ያለኸው? በትሩን ያስጨበጠህ አርቲስትም ብትሆን ትራ ጉርሻ የሚሸጥባት አዲሳአባን ዞር ዞር ብለህ አይተሀት ይሆን? እርግጠኛ የእለት ቀለብህን ከሚሰፍርልህ ሸራተን አዲስ ወጣ ወጣ ብትል ይህን ያገ እውነት ትመለከት ነበር።

ኮማንደር ጥያቄውን ቀጠለ፤

"ለምነህና ምጣብ ሸጠህ በቀን ስንት ብር ታገኛለህ?

"አይ ጌታው እሱ እንኳን ትንሽ ነው። መቶ ብር አይሞላም ኮማንደር መቶ ብር ጻፈ።

"በቀን ስራህ ሰንት ታገኛለህ?

"ብዙ ጊዜ በኦንትራት እሰራለሁ። ሙሉ ቀን ከዋልኩ እስከ መቶ ብር" ኮማንደር 100 ብር ጻፈ።

ወደ እኔ ዞሮ "ጥያቄህ ተመለሰ?" ብሎ ጠየቀኝ።

"ባላውቅ ይሻለኝ ነበር" ስል ምላሽ ሰጠሁት።

***

ምእራፍ ስምንት

"ህገ -መንግስት በጠረባ !"

"ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም የማለት መብት ፍርድ ቤቶች የላቸውም "
(አሊ አብዶ)

"...ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም ብሎ ብይን የሚሰጥ ፍርድ ቤት ይሌለባት
ብቸኛ ሀገር ኢትዮጵያ መሆኗን ጠፍቶኝ አይደለም!"
(ያልታወቀ ዳኛ)

ታላቋ ቀን!

ወቅቱ ጥቅምት 1994 ዓ.ም ነበር።

የአዲሳባ ምክር ቤት አዳራሽ አስቸኳይ ጥሪ በተደረገላቸው የፌዴራል
ከተማ ካድሬዎች፣ የፍርድ ቤት ባለስልጣናትና ዳኞች፣ የፓሊስ አዛዦ
ተሞልቷል... ከዚህ ቡተጨማሪም የአካል ጉዳተኛ በሆኑት ግለሰብ የሚመራ
የአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት ሀላፊዎች በስብሰባው ተገኝተዋል።

አጀንዳው "መሬት ለአልሚዎች በማስረከብ ዙሪያ ያጋጣሙ ችግሮች
መፍትሄዎቻቸው" የሚል ነበር... ህግ አውጭውን፣ ተርጓሚውና አስፈፃሚ
በጥድፊያ ያገናኘው አጀንዳ።

የፕሬዝዳንት አሊ አብዶ ፕሮቶኮል ሹም ጤናዳም በየሲከ
የመጡትን ሹማምንት አቴንዳንስ ወሰደ።ሁሉም መግኘቱ ሲረጋገጥ በውስጥ
በኩል የፕሬዝዳንቱን ቢሮና አዳራሽ በምትገኘው በር አሊ አብዶ፣ የፊደ
ጉዳዮች ሚኒስትር አባይ ፀሀዬ ፣የፊዴራል ፓሊስ ኮሚሽነሩ ወርቅነህ ገበየ
የፍርድ ቤቶቹ ምፖፕሬዝዳንቶች መንበረ ፀሀይና ደሳለኝ፣ የአዲሳባ ፖ
ኮሚሽነሩ በፍቃዱ ዶሌራ ተከታትለው ገቡ።

የህግ ምሁሩ ኮሚሽነር በፍቃዱ አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠ። ሦስ
ቀላል ሰው ስለሆነ እንግባባለን። በከተማዋ የፀጥታ ስራዎች ሳምንታዊ ግም
ላይ እንገናኝ ነበር።ህገ ወጥ ግንባታ የመከላከል ስራ በጥምር ሰርተ
የህይማኖት ተቋማትን አብረን አፍርሰናል። አስገንበተናል።

የኮሚሽነር ሰላምታ አሰጣጡ የወትሮ አልሆንብኝ ሲል ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ "እይዞህ! የምን መበሳጨት ነው! ግፉ ቢል ወደ ጠመኔህ ትመለሳለህ..." አልኩት።

በአንድ ወቅት የከተማዋ ካድሬዎች በተገኙንበት የሀገር ውስጥ ደህንነት የበላይ ሹመ ጊታቸው አሰፉ "የአሮሞ ጠባብነት አለብህ!... የትራፊክ ጽ/ቤት ን በእነግ በምንጠረጥራቸው ሰዎች አጥለቀለከው" ብሎ ሳምኑቱን ሙሉ አስጨነቀው። ርግጥም የትራፊክ ፓሊስ አለቃነት ለአሮሞዎች ተለይቶ የተሰጠ ይመስል ነበር። እጅግ በጣም የሚገርመው የደህንነት ሹመ የአሮሞ ልጆች የተከማቹበትን ቦታ ለይቶ የሚያውቅ ህሊና ከነበረው ሌሎች ቦታዎች ላይ እነማን እንዳሉም ጠንቅቆ ያውቃል ማለት እንደሆነ አዙሮ አለማሰቡ ነበር። ኮሚሽነሩ በጊታቸው አይታ ተበሳጭቶ የመጣ ይምጣ በሚመስል መልኩ፣

"...የፓሊስ ዋና ስልጣን የመከላከል ሀላፊ መሆን እንጂ መኪና መጠበቅ አይደለምኒ የወንጀል መከላከሉ ደግሞ ከፌደራል አስከ አዲሳባ በማን እንደተያዘ ይታወቃል!... የሚሰማህን ንገረኝ ካልከ ከዚህ አስቀያሚ ስራ ወደ ጠመኔዬ ብመለስ ይሻለኛል" የሚል ምላሽ ሰጠ። ያንን ለማስታወስ ነበር በምከር ቤት አዳራሽ ያነሳሁበት።

"የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትንገር ሆኖብኝ ነው" በተራው ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ መለሰልኝ።

"አሊ አብዶ ባለበት ስብሰባ ምን ጥሩ ነገር ትጠብቃለህ?" ኮሚሽነሩ ለአሊ አብዶና ምክትሉ ካሊድ አብርሀማን ከፍተኛ ንቀት እንዳለው አውቃለው። በከተማዋ እየተዛመተ ያለው ህገወጥነት ምንጮቹ እነሱ እንደሆኑ ደጋግሞ ይናገራል።

"ኧረ ጉዳዩ ከእነሱ በላይ ነው! ... ተወኝ ባከህ! ... የህግ ሀ - ሁ የቀመሰ ሰው በፓሊስ ሹመት ደጃፍ ማለፍ የለበትም። ዘላለሙን ከራሱ ጋር እንደተጣላ ይኖራል!" አለኝ።

አሊ ጉሮሮውን ሞርዶ ስብሰባውን ጀመረ።

አስተዳደሩ በኢንቨስትመንት ደረጃ ከፍተኛ እምርታ እንዳስመዘገበ፣ ይህ አመርቂ ለውጥ የመጣው በሶስቱ የመንግስት አካላት የተቀናጀ ጥረት እንደሆነ፣ ለዚህ ተስፋ ሰጪ ውጤት በከተማዋ ህዝብ ስም ምስጋና ማቅረብ እንደሚፈልግ ተቆጥቶና ፊቱን አጨማዶ ገለፀ። ይህም ሆኖ በአንዳንድ የልማት ስራዎች ላይ በተለይም መሬት በማዘጋጀት ለአልሚዎች በመስጠት ሁሪያ ችግሮች እያጋጠሙ በመሆኑ ልማቱ እየተጓተተ መሆኑን አስረዳ። አባይና ኮሚሽነር ወርቅነህ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ንግግር አደረጉ።

አሊ አጋጥመዋል ያላቸውን አንቅፋቶች መዘርዘር ጀመረ፡ - የከተማው ፓለቲካ ተሿሚዎች ህዝበኝነት፣ የፓሊስ ቁርጠኝነት ማጣት፣ የፍርድ ቤቶች ዳተኝነት እንደሆነ ገለፀ። በተለይም ዳኞች ለትንሽም ለትልቁም "ሁከት ይወገድልኝ " መስጠታቸው ልማቱ ተንገራግጮ እንዲቆም እያደረገው እንደሆነ ተናገረ።

ከተሰብሳቢው ውስጥ የማጉረምረም ድምፅ ተሰማ። አሊ ተልባ ቢንጫጫ በሚመስል መንገድ ጉምጉምታውን ወደ ጉን ትቶ የችግሩ ዋነኛ ምንጭ የሆነው "ሁከት ይወገድልኝ" የሚለው የፍርድ ቤት ወሳኔ ያስከተለውን ችግር ለመወያየትና ለቀጣይ መፍትሄ ለማስቀመጥ እንደሆነ፣ በዚህ የዳኞች ውሳኔ ሰለባ በመሆን ለከፍተኛ ኪሳራ እየተዳረጉ ያሉ ልማታዊ ባለሀብቶች በስብሰባው ስለተጋበዙ ዘርዘር ያለ ማብራሪያ እንደሚሰጡ ገለፀ። የአያት ፀኖሪያ ቤት ስራ ድርጅትን ወክለው የመጡት ግለሰብ ቅሬታቸውን እንዲያቀርብ በክብር ጋበዘ።

የአያት ተወካይ አንድ ሳምሶናይት መሉ ዶሴዎችን ለተሰብሳቢው በማሳየት ንግግራቸውን ጀመሩ። ሰውየው ፋይል አያገላበጡ የመጀመሪያው የፍርድ ቤት ክስ በንባብ ማሰማት ሲጀምሩ ከተሰብሳቢዎች መሀከል "ሰነ ስርአት" _ "ሰነ - ስርአት" የሚል ቃል ከየቅጣጫው ተሰተጋባ።

አሊ እንደለመደው የከተማውን ካድሬ የሰበሰበ መስሎት፣
"እንድ ሰው የጀመረውን ሳይጨረስ ማቋረጥ አግባብ አይደለም" ባይሆን የአያት ተወካይ አጠር አድርገው ፍሬ ፍሬውን ይግለፁ" በማለ ተሰብሳቢውን በቁጣ ገሰፀ።

"ሰነ - ስርአት!"፣ "ሰነ - ስርአት!"... የማያቁም ተቃውሞ።

አሊ አባራው ታየ!

ፊቱን ወደ አባይ አዙሮ በምን ይሻላል አይኑ ገረመመው። የሰነስርአ ጥያቄ ላነሱት አድሉን እንዲሰጣቸው ፈቀደለት።

የመጀመሪያው ተናጋሪ ዳኛ መሆኑን አስቀድሞ በመግለፅ ሰብሰባው ወጥ መሆኑን ማስረዳት ጀመረ።እንዲህ በማለት፣

"በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ በፍርድ ቤት በተ ብይን ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠት የፍርድ ሂደ ያጨናግፈዋል ተብሎ ስለሚታሰብ የተከለከለ ነው። በተለይም ለፍትህ ስር አጋዥ ይሆናሉ ተብለው ከሚታሰቡት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣ የፓሊሰና የፀጥታ ሀይሎች ከዳኞች ጋር የከስ ጭብጦችን እያነሱ መዝ የፍርድ ቤቶችን እጅ አንደ መጠምዘዝ ይቅጠራሉ።"

ዳኛው የሰጠው አስተያየት ስላልገባኝ አጠገቤ የተቀመጠውን ኮሚሽነር ጠየኩት።

"ይህ የህግ ሀ - ሁ ነው። በፍርድ ቤት በተያዘ ጉዳይ ላይ የፓለቲካ ስልጣኑን የያዘው፣ ፓሊስና ሌሎች የፍትህ አካላት ከዳኛ ጋር ቁጭ ብለው አይነጋሩም። ዳኛው አንዳለው የፍትህ ሂደቱን ያጨናግፈዋል ተብሎ ይታሰባል። ከውሳኔ በኋላ ብዙም ችግር ስለማያመጣ በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ሳይቀር አስገብተው እንደመማሪያነት የሚጠቀሙበት አሉ።" ብሎ ምላሽ ሰጠኝ።

"እንድ ዳኛ በግልፅ የተገፈለትን አስከተረገመ ድረስ ምን ለውጥ ያመጣል?"

"ህግ ማቲማቲከስ አይደለም... አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ብለህ አታቁምም"

"አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ብቻ ነው ያለህ ማነው? ሶስት የሚሆንበት ጊዜ አለ... ሂሳቡን ለባለቤቱ ተውና ህጉ እንዴት እንደሚጨናገፍ በምሳሌ አስረዳኝ።"

ኮሚሽነር እንዲህ በማለት ምላሽ ሠጠኝ።

"የምታውቀውን ልንገርህ። እነ ስዬ አብርሀ በሌብነት ተከሰው ፍርድ ቤት እየተመላለሱ እያለ አቶ መለስ በኢቲቪ ቀርቦ ሌበነታቸውን በዝርዝር አቀረበ። አንድ ተጠርጣሪ ከብይን በፊት እንደ ንጹህ ይቆጠራል የሚለውን አፈረሰ።የፍርድ ውሳኔው አስቀድሞ በፓለቲካ ባለስልጣናቱ ተሰጠ። ተናጋሪው በሀገሪቷ የስልጣን ማማ የመጨረሻው ጫፍ ላይ የተቀመጠ በመሆኑና የዳኝነት በርእቱ ጠንካራ ስላልሆነ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቃላቶች ብይኑን ሊያዛቡት የሚችሉበት እድል ተፈጠረ። የህግ ሙያተኞችን ያበሳጨው አነስዬ ሌባ ስላልሆኑ ሳይሆን የአቶ መለስ ዳኛ ሆኖ መገኘት ነበር"

እንደገባኝ ነግፈው ጅሮዬን ወደ ቁጣዬ አስተያየት ሰጪ አሻገርኩ።

ሁለተኛው ተናጋሪ በተመሳሳይ ዳኛ መሆኑን አስቀድሞ በመግለፅ የእያት ተወካይ በንቡብ እያሰሙት የነበረውን ጉዳይ በመዳኘት ላይ ያለው እሱ መሆኑን ተናገረ። በነገድጓድ ድምፁ፣

"... ሌላው ቢቀር ከሳሽና ተከሳሽ በአንድ መድረክ በሲሉበት የአንድ ወገን አቤቱታ አዳምጦ አስተያየት ለመስጠት ህሊናችሁ ማሰቡ በራሱ ጥያቄ ሆኖብኛል!... ይህንን ስብሰባ የጠራችሁ አካላት የዜጐች በፍርድ ቤትና ፍርድ ቤት የመዳኘት መብት ጥሳችኃል" ብሎ ተናገረ።

አሊ አብዶ በበኩሉ፣

"ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም የማለት መብት ፍርድ ቤቶች የላቸውም በማለት በአቶ መለስ የተፃፈውን የዲሞክራሲ ጥያቄ በኢትዮጵያ

የማ‌ሊለውን ሰነድ አነበነበ።

"ከቡር ፕሬዝዳንት! ህገ - መንግስት ተጥሷል/አልተጣሰም ብሎ ብ የሚሰጥ ፍርድ ቤት የሌለባት ብቸኛ ሀገር ኢትዮጵያ መሆኗን ጠፍ አይደለም።ሌላው ቀርቶ ህገ - መንግስትን በተመለከተ ብይን የሚሰ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሰጥ ከአራት ሚሊዮን በላይ የሆነው የአዲሳባ ህዝ ሆነ ከቡርነትዎ እንዳልተወከሉ አውቃለሁ።ነገር ግን የዜጐችን በፍርድ የመዳኘት መብት የሰጠው ህገ - መንግስት በጠረባ ሲመታ ለማየት ህሊ ስላልፈቀደ ነው።" በማለት ሁለተኛው ዳኛ የመልስ ምት ሰጠ።

ትንሿ አዳራሽ በድጋፍና ማጉረምረም ተነቃነቀች።

አጠገቤ የተቀመጠው ኮሚሽነር በተራው ጠጋ ብሎኝ፣

"እንጀቴ ቅቤ ጠጣ! እኔ ለወንበሬ ፈርቼ ያልተናገርኩትን ተማሪ አፈረጠት። ይሄ አድርባይ አለቃህ እያየሁት ሰመጠ!" አለኝ።

በዚህ መልኩ መቀጠል እንደማያዋጣ የተገነዘበው አባይ ፀሀዬ ና ሰአት ረፍት እንድንወስድ በማድረግ ስብሰባው እንዲቋረጥ አደረገ። በሻይ ሰ የፕሬዝዳንቱ ፕሮቶኮል ጤናአዳም አየዘረ ስብሰባው ላልተወሰነ ጊዜ እንዳ መደረጉንና ለወደፊቱ አስተዳደሩ እንደሚያሳውቅ በመግለፅ ተሰብሳቢው መጣበት እንዲመለስ መልእክት አስተላለፈ። የከተማና ዞን ካድሬዎች ወደ እንድንቀር በተናጠል ነገረን። አብሮኝ ሻይ ሲጠጣ የነበረው ኮሚሽነር በፍ "በል ማክሰኞ እንገናኝ። ታዲያ እንደ ቆምጬ አንባው ቀኝ እጅህን ለማው ተዘጋጅ!" በማለት ተሰናብቶኝ ሔደ።

ወደ ሰብሰባ ተመለስን።

ከመዲናይቱ ካድሬዎች ውጭ አባይ፣ ኮሚሽነር ወርቅነህ፣ የፍ ቤቶቹ ምክትል ፕሬዝዳንት የሆነው ደሳለኝ እና የአያት ድርጅት ተወካ ተገኙ።

አቶ ደሳለኝ የጠበቀው ነገር እንዳጋጠመውና አሱ የሚመራው የዳ ስርአት በፀረ-ኢህአዴግ እንደተወረረ ገለፀ። መፍትሔ ይሆናል የሚያስበው፡ በህገ - መንግስቱ መሰረት መሬት የህዝብ በመሆኑና የህ ውክልና ያገኘው ያለተዳደሩ ምክር ቤት በአስቸኳይ ተሰብስቦ ከዚህ ቀ በፍርድ ቤቶች የሚሰጠው "ሁከት ይወገድልኝ" የሚቀርበትን ውሳኔ ማስተላ እንደሆነ አስረዳ። አከሎም የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ህግ አውጣ ያወጣውን አዋጅና ህጐች የመተርጐምና በዛ ብቻ የመመራት ግ እንዳለበት ሰፊ ማብራሪያ ሰጠ። አገራችን የምትከተለው የኮንትኔንታል (ሲ ህግ ዘርፍ መሆኑን ነገረን። በዚህ መሰረት ዳኞች አስቀድሞ በህግ አውጣ